# መጣበቦች

ራሶቻችን ዝቅ አድርገን እንደቆምን እንቆይ።

ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እያመንን ብቻ ነው። እንድናምን ብቻ ነግረኸናል፡ አሁንም እናምናለን። እምነታችንን ለሚያጸናው፡ አስቀድመን ለስማነውና ላየነው ነገር ምስጋናንና ውዳሴን እናቀርብልሃለን። የተቸገሩትን ለማገልገል ዳግም ስለሰጠኸን ሌላ እድል ምንኛ እናመሰግንሃለን። አሁንም አምላክ ሆይ፡ እንደ ተስፋ ቃልህ ዛሬ ማታ የሚያስፈልገንን እንድታሟላልን፡ እጸልያለሁ። በኢየሱስ ስም እንለምናለን። አሜን።

2 የተነሳውን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይዘን በዚህ ተበርናክል ውስጥ ዳግመኛ ለመገኘት ስለበቃን፡ ዛ—ዛ... ዛሬ ማታ እጅግ ደስተኞች ነን። ጥቂት ዘግይቼ ነበር። አሁን ከሚሺጋን የመጣ ልዩ የሆነ አስቸኳይ-ጉዳይ ገጥሞኝ ነበር። ጌታም በዚሁ ቅጽበት ለእርሷ ድንቅ ነገር አደረገላት። እንዴት፡ ሁሉንም ነገር እንደሚያውቅና እንደሚያስቀምጥ... ለእርሱ መንገር አያስፈልግም፥ እርሱ ያውቃል፡ ምን እንደሆነ እርሱ ያውቃል። ስለሆነም እጅግ አመስጋኞች ነን። ሰዎቹ እዚህ ለመድረስ ቀኑን ሙሉ መኪና ሲነዱ ውለዋል። ከዚያም፡ ስለዚህም፡ ምስጋናችን የላቀ ነው። አሁን፡ አትርሱ...

ይህ ቴፕ በርቷልን? [ወንድም ኔቭል፡ "የመብራቱ መቆጣጠሪያ ነው" አለ።—አርታዒ።] ኦህ፡ የመብራት መቆጣጠሪያ። ገባኝ።

በ—በሚመጣው ሳምንት፡ ረቡዕ ማታ፡ እንዲሁም በመጪው እሁድ ጠዋትና፡ እሁድ ማታ የሚኖሩትን አገልግሎቶች አትርሱ። በአካባቢው፡ ጎረቤት ከሆናችሁ፡ እዚህ ብትገኙ በእርግጥ ደስ እንደሚላቸው አውቃለሁ።

አሁንም፡ ወደ ሌላ ስፍራ በምጓዝበት ጊዜ፡ ጸልዩልኝ፡ በቅርቡም ዳግም እንደምመለስ ተስፋ አደርጋለሁ።

3 ስላደረጋችሁልኝ መልካምነትና ትዝታዎች ሁላችሁንም ላመሰግን እወዳለሁ። አንድ ወንድም በጆርጂያ ከምትገኝ አንዲት ትንሽ ቤተክርስቲያን አዲስ ሙሉ ልብስ ልኮልኛል። እ—እነዚያም ሰዎች... በእውነት አስደናቂ ነው። ባለፈው ሳምንት በእረፍት ጊዜ አብሬያቸው ለነበርኩት፡ በኬንታኪ ለሚገኙት ሰዎች ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ። ጌታም በዚያ ላደረገልን ሁሉ፡ እርሱ ያደረገው፡ ያየነው ታላቅና፡ ብርቱ እጁ ነው።

4 አሁን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ዳግም እንደምናያችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡ ለስብሰባ ወደ ኒው ዮርክ በመሄድ፡ በዚህ መንገድ እንደተመለስኩ ወዲያውኑ ማለት ነው። ይህም ከወንድም ቪክ ጋር በሰቶን ቤተክርስቲያን ይሆናል፡ ኖቬምበር አስራ ሁለት፡ እንደሚጀምር አምናለሁ። ከተባለው ጊዜ ጥቂት ቀናት ቀደም ብለን፡ በዚህ እንገኛለን።

ከዚያም ዳግም ተመልሰን፡ ከወንድም ጃክ ሙር ጋር፡ ወ—ወደ ሽሬቭፖርት፡ ሉዊዚያና እንሄዳለን። ይህም ታንክስጊቪንግ፡ ታንክስጊቪንግ ሳምንት፡ በሽሬቭፖርት ይሆናል ማለት ነው። እዚያ ኋላ በማስታወቂያው፡ በስሌዳው ላይ፡ ያለ ይመስለኛል።

5 ከዚያም ከገና በዓል በኋላ ከአንዳንድ የደቡብ ወዳጆች ጋር እንደምንሆን ተስፋ እናደርጋለን። በጃንዋሪ ውስጥም በፊኒክስ እንሆናለን። ከዚያም ከባህር ማዶ የሚደረጉ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት እንድንችል፡ የባህር ማዶ ጥሪን እንጠብቃለን። አሁን በእነርሱ ላይ እየሰሩ ይገኛሉ፡ ባለፈው ወር ውስጥ፡ ወንድም ቦርደርስ፡ እየተጻጻፈ ነበር፡ ዝግጁ ማድረግ እንደቻልን ወዲያውኑ የሚጀምር የተሟላ የዓለም ጉብኝት ለማዘጋጀት ነው፡ ዳሩ ግን ሁኔታዎችን መጠበቅ ግድ ይለናል።

6 በዚያ ሕዝቡ እጅግ በጣም ብዙ ስለሆነ፡ በህንጻዎች ውስጥ ልናስገባቸው አንችልም፥ እንዲሁ መሬት ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ ብቻ አለብን። ከዚያም አንዳንድ ጊዜ ቁጥራቸው ከፍ ይላል፡ ቁጥሩ ለማመን የሚያዳግት ነው፡ አንዳንዴም እስከ አምስት መቶ ሺህ ይደርሳል። ይኸውም በአንድ ስብሰባ ግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ ማለት ነው፥ በብዙ ቀናት ውስጥ በስብሰባው ላይ ምን ያህል እንደተገኙ ሳይሆን፡ በአንድ ስብሰባ ላይ ነው። ታውቃላችሁ፡ ብዙውን ጊዜ ወንጌላውያን በስድስት ሳምንታት ውስጥ ምን ያህል ሰዎች እንደተገኙ ይቆጥራሉ። አያችሁ? ነገር ግን እኛ—በዚያ ቀን ብቻ፡ በዚያ አንድ ጊዜ፡ ምን ያህል እንደተገኙ ብቻ እንቆጥራለን። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ የሚያስቀምጧቸው ስፍራ የለም፡ ታውቃላችሁ፡ እንዲሁ መሬት ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ ግድ ይላል።

ዝናብ በማይዘንብበት ዶፍ በማይወርድበት ወቅቶች ማድረግ አለብን። እነዚያ ምስኪን ሰዎች እዚያ ተቀምጠው... ሴቶች ጸጉራቸው ወደ ታች እየተንጠባጠበ እዚያው ሲቀመጡ አይቻለሁ፡ ጥሩ-ልብስ የለበሱ ሰዎች፡ ቀኑን ሙሉ በዚያ ዝናብ ውስጥ እ—እንዲሁ ይቀመጣሉ። እንዲሁ እዚያው ይቀመጣሉ፡ ዝናቡም ይወርዳል፡ ነጎድጓድ፡ መብረቅ፡ እንዲሁም አውሎ ነፋስም ይነፍሳል፡ እነርሱም እርስ በእርሳቸው እንደዚያ እየተጋፉ፡ እዚያው ተቀምጠው፡ መጥታችሁ እስክትጸልዩላቸው ድረስ ይጠብቃሉ። አያችሁ? አሁን፡ እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን እምነት እንደሚያከብር ታውቃላችሁ። ያከብረዋል።

7 እግዚአብሔር እንዲያከብረው የሆነ ነገር ማድረግ አለባችሁ። አያችሁ? ለእርሱ ታሳዩታላችሁ። ሁሉም ነገር በቀላሉ የሚሰጣቸው ሰዎች፡ ብዙውን ጊዜ... ለ—ለዚያ ነገር ምንም አያደርጉም፡ አያችሁ። ማድረግ ያለባችሁ... ስጦታው ነጻ ነው፡ ያ እውነት ነው፡ ነገር ግን ማ—ማድረግ አለባችሁ...

8 እንደዚያ ይመስላል፡ ታውቃላችሁ፡ እንዲህ እንደሚሉት ነው፡ "የብር ማንኪያ ይዞህ ከተወለድክ፡" "አታከብረውም፡" ሲባል ሰምታችኋል። ለፍታችሁ ስታገኙት ግን፡ የነገሩን ዋጋ ታደንቃላችሁ።

9 አሁን እዚያ ቴፕ የምትሰሙ ሰዎች፡ ያ—ያ... አሁን የማስበው...

ዛሬ ጠዋት፡ የዛሬው ጠዋት መልእክት፡ ለእኔ፡ ለመላው አገልግሎቴ ዋናው ማሳረጊያ መልእክት ነበር፥ ዛሬ ጠዋት፡ አያችሁ፡ ለመላው አገልግሎቴ ዋና ማሳረጊያ መልእክት ተናግሬያለሁ። አንድ ቀን እንዴት እንደመጣ እነግራችኋለሁ። ነገሮች ሁሉ ለወራትና ለወራትና ለወራት ያህል፡ እስከዚያኛው መልእክት ድረስ፡ ወደዚያ ስፍራ ለመምጣት ሲንቀሳቀሱ እንደነበር አውቃለሁ። ያ የነገሩ-ማጠቃለያ ጊዜ ነበር፡ አያችሁ። እንዲሁም...

10 አሁን ምልክቱ ምን ማለት እንደሆነ እንደተረዳችሁ፡ እርግጠኛ ነኝ፡ ወይም ተስፋ አደርጋለሁ። አያችሁ? ምልክቱ ደሙ እንደተቀባ የሚያሳይ ማረጋገጫ ነው። ይህም፡ የተጠየቀውን፡ በእግዚአብሔር የተጠየቀውን ዋጋ፡ ኢየሱስ የገዛ ደሙን በማፍሰስ ያንን ዋጋ ከፍሏል። ያንን አድርጓል። ከዚያም፡ ከሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ መጣ። ደሙም በእናንተ ላይ ሲቀባ፡ መንፈስ ቅዱስ ዋጋችሁ እንደተከፈለ የሚያሳይ ምልክት ነው፥ እግዚአብሔር ተቀብሏችኋል፡ ምልክቱም ያ ነው። አስታውሱ፡ ያ ምልክት ነው። አሁን፡ ይህን የማያደርጉ ብዙ ሰዎች አሉ፡ ያ—ያ ምልክት ምን እንደሆነ አያውቁም፡ አያችሁ። ሁሉም እንዲያገኙት፡ ማንም እንዳላወቀው አድርጋችሁ ማቅረብ አለባችሁ፡ አያችሁ።

11 ልክ ደህንነትን እንደምንሰብከው ነው፡ ደህንነትን ለሁሉም ሰው በሚሆን መንገድ መሰበክ አለብን፡ ለሁሉም ሰው ነው፡ ቢሆንም፡ ለሁሉም እንዳልሆነ እናውቃለን። መለኮታዊ ፈውስን ለሁሉም ሰው መሰበክ አለብን፡ ሆኖም ለሁሉም እንዳልሆነ እናውቃለን። አያችሁ? ኢየሱስ የመጣው ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በቤዛነት መጽሐፍ ውስጥ የነበሩትን ለማዳን ነው። እርሱ የመጣው እነርሱን ለማዳን ብቻ ነው። እነርሱ እነማን እንደሆኑ፡ እኔ አላውቅም። አያችሁ? ነገር ግን... ለሁሉም ነው ካላላችሁ በስተቀር ማንም እምነት ሊኖረው አይችልም፥ እንደዚያም ነው፡ እግዚአብሔር ከጠራቸው በስተቀር ማንም ሊመጣ አይችልም። ያ እውነት ነው። ስለዚህ የማይድኑ ብዙ ሰዎች አሉ። ስለዚህ ነገር እናውቃለን። እነርሱ፡ ደህና፡ እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፡ እንደማይድኑ ያውቅ ነበር።

12 የማይፈወሱ ብዙዎች አሉ፡ አያችሁ፡ ብዙዎች አይፈወሱም። በቃ አይችሉም፡ ሊጨብጡት አይችሉም። ምን እንደሆነ አያውቁም። ብዙዎች ይፈወሳሉ። ዳሩ ግን ለሁሉም ሰው እንደሆነ እንሰብከዋለን፡ ምክንያቱም ያ ሰው ማን እንደሆነ አናውቅም፥ ብቻ አናውቅም። ዳሩ ግን ያ ለማንም ነው፡ ሆኖም አንዳንዶች ያንን እምነት ሊጨብጡት አይችሉም።

13 አሁን፡ ስለዚህ ምልክትም እንዲሁ ነው። ምልክቱን፡ በመንገዱ ሁሉ ስለ ምልክቱ ተናግረናል፡ አሁን ግን የምልክቱ መገለጥ ነው። አያችሁ?

14 አሁን፡ አንዳንዴ ተቀብለነዋል። ሉተራውያን፡ "ቃሉን መቀበል፡ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ መቀበል ነው" ብለው ተቀብለውታል። ሜቶዲስቶች፡ "ለመጮህ የሚያስችል በቂ ደስታ ሲያገኙ፡ ይኸው ነው" አሉ። ጴንጤቆስጤ ደግሞ፡ "በልሳን ከተናገራችሁ፡ ከዚያም አግኝታችሁታል" ይላሉ። ይህ ሁሉ ስህተት መሆኑንም ደርሰንበታል። አያችሁ?

ምልክቱ ምልክት ነው። አንተና ክርስቶስ እንደ ግለሰብ አንድ መሆናችሁ ነው። አያችሁ? መንፈስ ቅዱስ ነው፡ የርሱ ሕይወት በእናንተ ውስጥ ሆኖ፡ የራሱን—የራሱን ሕይወት በእናንተ ውስጥ ሲሰራ ነው። ይህም ለሀብታሙ፡ ለድሀው፡ ወይም ለሚቀበለው ሁሉ ነው። አሁን ልብ በሉ፡ ምልክቱ ማለት እናንተ...

15 ወደ ባቡር ኩባንያ ሄዳችሁ የጉዞ ትኬታችሁን ትገዛላችሁ። ዋጋ አለው፡ የብር መጠን። በ—በዚህ የአውቶቡስ መስመር፡ ወይም በባቡር፡ ከዚህ ወ—ወደ ቻርለስታውን፡ ኢንዲያና ለመጓዝ፡ ሃምሳ ሳንቲም ያስከፍላል እንበል። እንግዲህ፡ አሁን፡ ኩባንያው ምልክቶችን ያደርግባቸዋል... አያችሁ? አሁን፡

የምታደርጉት ነገር፡ ወደዚያ ትሄዱና አንድ ሰው የጉዞ ትኬታችሁን፡ በሃምሳ ሳንቲም ይገዛል። ያ ባቡር ወደሚሄድበት መዳረሻ ድረስ፡ በዚያ ባቡር ላይ የመሄድ መብት የሚሰጣችሁን ምልክት ይሰጧችኋል። አያችሁ? ያ ይሰጣችኋል... ያ ምልክት ነው።

16 አሁን፡ በዚህ ጉዳይ፡ ደሙ ምልክት ነበር። በትክክል፡ መቀባት ነበረበት፡ ምክንያቱም የተጠቀሙት ኬሚስትሪው ብቻ ነበር፡ ምክንያቱም የበግ ደም፡ የእንስሳ፡ የበግ ደም ነበር። ስለዚህ በደሙ ውስጥ የነበረው ሕይወት፡ ሕይወት ወጥቶ ነበር፡ ስለዚህ ደሙ ፈሰሰ። አያችሁ? ሕይወት ወጣ፡ ነገር ግን ወደ አማኙ ሊመለስ አልቻለም፡ ምክንያቱም እንስሳ ነውና። ነገር ግን አንድ የሚመጣ፡ ፍጹም መስዋዕት እንዳለ፡ ስለ በጎ ህሊና ብቻ ተናገረ።

እንዲሁም፡ ፍጹም ለማድረግ፡ ሙሉ ፈራጅ፡ የሰማይ አምላክ፡ መስዋዕት ሆነ፥ ፈራጅ፡ ዳኛ፡ ጠበቃ። አያችሁ? እርሱ መስዋዕት ሆነ። ከዚያም ሕይወቱ ሲወጣ፡ ይህም እግዚአብሔር የነበረው... በዚያም ያለውን ቃል፡ ከዬት እንደመጣ እንመልከት፡ "የዘላለም ሕይወትም እሰጣቸዋለሁ።" አሁን፡ በግሪክ... ለምሁራን እየተናገርኩ እንደሆነ አውቃለሁ። ሁለት ወይም ሦስት አይቻለሁ። አያችሁ? እኔም... እዚያ በግሪክ ያለው ቃል፡ ዞዊ ነው። Z-o-e፡ በግሪክ፡ "የእግዚአብሔር የራሱ ሕይወት፡" ማለት ነው። "እኔም **ዞዊ**፡ የራሴን ሕይወት እሰጠዋለሁ።" ክርስቶስና እግዚአብሔር አንድ ነበሩ።

17 ከዚያም፡ በክርስቶስ ውስጥ የነበረው ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ሦስተኛው አካል አይደለም፥ ነገር ግን ያው አካል፡ በመንፈስ ቅዱስ መልክ፡ በእናንተ ላይ ይመጣል፡ ይህም ሕይወታችሁና የጉዞ ትኬታችሁ እንደተከፈለ፡ እንደተቀበላችሁ የሚያሳይ ምልክት ነው። ያ ምልክት እስኪመጣ ድረስ፡ በዋናው መንገድ ላይ ለመሄድ አልተፈቀደላችሁም፡ በ—በአውቶቡስ መስመር ላይ... አይፈቀድላችሁም፥ ያንን ምልክት እስክታቀርቡ ድረስ ለመግባት አይፈቀድላችሁም፡ ያ ምልክት የጉዞ ትኬታችሁ ነው። አሁንም ደሙ እንደፈሰሰና በእናንተ ላይ እንደተቀባ፡ ዋጋው በእናንተ ላይ እንደተተገበረ ያሳያል፡ ደሙ በእናንተ ላይ እንደተቀባና እንደተቀበላችሁ የሚያሳይ ምልክት አላችሁ። አሁን ገባችሁ? ኦህ፡ ማይ! ኦህ!

18 አ—አሁን፡ ዝም ብሎ የተወሰነ ማረጋገጫ አይደለም። አያችሁ? "ወንድም ብራንሃም፡" ትላላችሁ፡ በአእምሯችሁ ውስጥ ይሰማኛል፡ አያችሁ፡ "እንዴት አውቃለሁ" ትላላችሁ?

ተመልከቱ፡ ምን ነበራችሁ፡ አሁንስ ምንድን ናችሁ? በዚያ ነው የምታውቁት። አያችሁ? ይህ ምልክት ከመተግበሩ በፊት ምን ነበራችሁ? ከተደረገ በኋላ ምንድናችሁ? ከዚህ በፊት ምኞታችሁ ምን ነበር፡ ከዚያ በኋላስ ምኞታችሁ ምንድን ነው? ያኔ ምልክቱ እንደተደረገ ወይም እንዳልተደረገ ታውቃላችሁ። እነዚህ ሌሎች ነገሮች ዝምብለው አብረው ይሄዳሉ። አያችሁ?

19 ነገሩ—ስለ እርሱ ማውራትና፡ "ልሳን ማረጋገጫ ነው፡" እንደማለት አይደለም። ለምሳሌ፡ እኔ አንድ፡ አንድ ጫማ ብገዛ፡ የጫማው ምላስ ጫማው አይደለም። ከጫማው ጋር አብሮ ይመጣል እንጂ፡ አያችሁ። ከጫማው ጋር አብሮ ይመጣል። አያችሁ? አሁንም፡ ምልክቱም ልክ እንደዚሁ ነው። ምልክቱ ክርስቶስ ነው። ነገር ግን በልሳን መናገር፡ አጋንንትን ማውጣት፡ እነዚህንም

ነገሮች ማድረግ፡ እና መሰበክ፡ ወይም ሌላም ነገር ቢሆን፡ እርሱ እዚያ እንዳለ የሚያሳይ ማስረጃ ነው፡ እውነት ነው፡ ነገር ግን ያ—ራሱ አይደለም። አያችሁ፡ የእሱ ስጦታ ነው። ይህንን ብነግራችሁ...

20 "እ—እፈልግሃለሁ፡ ወንድም ብራንሃም፡" ትላላችሁ፡ ስጦታንም እሰጣችኋለሁ፡ አያችሁ። መልካም፡ ያ እኔነቴን አይወክልም፡ ያ ስጦታዬ ነው።

ልሳን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው፡ መንፈስ ቅዱስ አይደለም፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው።

21 ዲያብሎስም ከነዚህ ነገሮች ማናቸውንም ሊያስመስል ይችላል፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችልም። አያችሁ? እነዚህን ስጦታዎች ሊያስመስል ይችላል፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችልም።

መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ደሙ እንደተተገበረ የሚያሳይ ምልክት ነው፡ ምክንያቱም ከመቤዠት መጽሐፍ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ደሙን ይከተላልና። አያችሁት? የእርሱ መምጣት ዓላማ ያ ነበረ። በየዘመናቱም የተከተለው ያንን ነው። ወደ ፊት እንዲመጣ ለማየት፡ በየዘመናቱ ያንን ተከትሏል፡ ያለ እኛም ፍጹማን ሊሆኑ አልቻሉም። አሁን ደግሞ መላው መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን ይጎበኛል፡ እግዚአብሔርንም በሰው ሥጋ ያደርጋል፥ ከሰዶም በፊት እንዳደረገው፡ በዚያ የነበረው መቃጠል፡ ምሳሌ ነበረና። ከዚያም፡ ለአብርሃም፡ ተገለጠለት።

22 በዘመናት ውስጥ በቤተክርስቲያን ዘመናት ውስጥ፡ ያላደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ፡ አሁን እያደረጋቸው ነው። ወደ ቃሉ ይመልሳል፡ ምክንያቱም መልእክቶቹና መልእክቶቹና መልእክቶቹ በመላው ቃል ውስጥ መጠቅለል አለባቸው። በመጨረሻዎቹ ቀናትም፡ ሰባቱ ማኅተሞች መፈታታቸው፡ በውስጡ የተተወውን ነገር ሁሉ ለመሰብሰብ፡ ሁሉንም በአንድ ታላቅ የሙሽራይቱ አካል ውስጥ ለማድረግ ነበረ፡ በዚያ ወደ ኋላ የኖሩት ይህች ቤተክርስቲያን ፍጹም እስክትሆን ድረስ ፍጹማን አልነበሩምና፡ ይህ የሙሽራይቱ ቡድን በመጨረሻዎቹ ቀናት፡ ወደ ውስጥ እንዲያስገባቸው፡ ሁሉም በአንድነትም እንዲነጠቁ ነው። አያችሁ?

23 ምልክቱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በመካከላችን ነው። ያንን ማክበር ይገባናል። ራ—ራ—ራ—ራሳችንን በበቂ ሁኔታ ማዋረድ አንችልም። ጫማችሁን ማውለቅ፡ ወይም በጉልበታችሁ መውደቅ፡ አያሰወግደውም፥ አ—አያረካውም፡ አይበቃንም፥ ነገር ግን የመንፈስን ፍሬ የሚያፈራ ሕይወት ነው እንጂ!

24 አሁን የመንፈስ ፍሬ ምንድን ነው? አያችሁ? ፍቅር፡ ደስታ፡ ሰላም።

25 ዛሬ ጧት ታስታውሳላችሁ? ለማዘጋጀት፡ መልእክተኛውን ከመልእክቱ ጋር ላከው። ቀጣይ ያደረገው ነገር፡ መልእክተኛውን ከመልእክቱ ጋር ከላከ በኋላ፡ ሊያጸና የእሳቱን ዓምድ ላከው። ከዛ በኋላ፡ ቀጣዩ ነገር፡ ህብረ-... ወይም ማጽናናት ነበረ። አያችሁ? ትክክል እንደነበረ አውቃችኋል፡ በሰላም ነበራችሁ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን። አያችሁ?

26 አሁን ዛሬ ማታ ለታመሙት እንጸልያለን፡ የጌታ እራትም ያላቸው ይመስለኛል። ጥ—ጥምቀት፡ የጥምቀት አገልግሎት ይኖራችሁ ይሆን?

[ወንድም ኔቪል፡ “የለም” አለ።—አርታዒ።] የጌታ እራት ብቻ፡ የጌታ እራት። ለጌታ እራት እንድትቆዩ እንፈልጋለን።

27 በሰላሳ-አምስት ወይም በ—በአርባ ደቂቃዎች ውስጥ ለመጨረስና ለጌታ እራት ዝግጁ ለመሆን አስበናል። አሁንም፡ ነገ የስራተኞች ቀን ስለሆነ፡ በመጠኑም ቢሆን ማረፍ ትችላላችሁ። አሁን፡ ያ ሃሳባችን እንደነበረ ተናግሬአለሁ፡ አያችሁ። ስንት ሰዓት እንደሆነ አናውቅም። ያንን በትክክል ማድረጌን እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ።

28 አሁን፡ ዛሬ ጠዋት ነግሬያችኋለሁ፡ ከእናንተ ጋር ባለመሆኔ፡ ዛሬ ጠዋት ሌላ የሁለት- ወይም የሦስት-ሰዓት መልእክት የነበረን ይ—ይመስለኛል። ነ—ነገር ግን ገ—ገና ጀምሬ ነበረ፡ ያንንም ለዛሬ ማታ ላስተላልፈው አስቤ ነበር፡ ነገር ግን እጅግ አሰደናቂ ነበረ። ሰዎቹ እንደገባቸው ወይም እንዳልገባቸው አላውቅም። በሁሉም ሰፍራ፡ እንደገባቸው ተሰፋ አደርጋለሁ። በዚያም ላይ አንዳንድ ጥሩ ቴፖች እንደነበሩ ተሰፋ አደርጋለሁ፡ ስለዚህ ሊተላለፍ፡ ሊታወቅ ይችላል፡ ከዚህ በፊት ካመጣሁት መልእክት ሁሉ ጋር፡ ያ በእርግጥ በእግዚአብሔር የታሰበ እንደሆነ፡ አምናለሁ፡ በሰተ... እርግጥ ነው፡ መደበኛው ተልዕኮ፡ እንደ ሰባቱ ማኅተሞችና ነገሮች፡ ያ ቀጥታ የእግዚአብሔር ቃል ነበረ። ስለሚሰበክ መልእክት እያወራሁ ነው፥ ያ እርሱ እንደነበረ አምናለሁ፡ አያችሁ፡ እነዛን ሰባቱን ማኅተሞች ለመከተል የሚያስፈልገው፡ ያ—ያ ነው።

29 አሁን ከሰባቱ ማኅተሞች በኋላ የመጣውን ተመልከቱ፥ የህዝብ መተባበር፡ የተባበሩ ምልክቶች፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚያበራው ቀይ መብራት፡ የሴቶች ውበት እየጨመረ የመምጣቱ ምልክት፡ እንዲሁም ወንዶቹ፡ የሚያደርጉት ነገር። እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ምልክቶች፡ ከዚያም ከሰባቱ ማኅተሞች ወዲህ ያሉትን መልእክቶች ሁሉ ወደ-ማጠቃለያው እዚሁ ይመለሳሉ። በዚህ በአንድ ነገር ተጠቃልሏል፡ ምልክቱ፡ ደህና መሆናችንን፡ አያችሁ፡ በእምነት ውስጥ መሆናችንን ራሳችንን መመርመርና ማየት ነው።

30 አሁን፡ ጌታ ይባርካችሁ። አሁንም ወደ—ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ከማለፋችን በፊት፡ ለታመሙት ለመጸለይ... ዛሬ ጥዋት ጠቀን ነበር፡ ባለፈው እሁድ ማታ፡ ተጸልዮላቸው የ—የ—የዳኑት፡ አሰቀድመው የተፈወሱት ሰንቶች እንደሆኑ ጠይቀናል፡ ባለፈው እሁድ ማታ በሰብሰባው ላይ የነበሩ፡ አሁን እዚህ ያሉ ሰዎች ሁሉም እጆቻቸውን አንስተዋል። አሁን፡ አንድ ነገር ነው፡ ትረዳላችሁ። አንድ የሆነ ነገር ነው... ይህም፡ ይህንን ለራሴ እየያዝኩት ነው።

31 አሁን እንደተነገረኝ፡ ከቺካጎ የመጣ አንድ ትንሽ ልጅ ነበረ፡ አንዲት ምሰኪን ወይዘሮ... ያቺ ሴት፡ ፔኪንፓው ናት፡ ፔክ-... ሚሰ ፔኪንፓው ከ—ከ... እሷ በጣም ጥሩ ክርሰቲያን እህት ናት። አንድ ሰውም አመጣች፡ እንደ ገባኝ ከሆነ፡ አ—አንድ ህጻን ልጅ፡ አንድ ትንሽ ልጅ ወይም እንደዛ ነገር ይዛ መጣች፡ ይህም... ሐ—ሐኪሞቹም እንኳን ምን እንደነካው አያውቁም ነበረ። ትምህርት ቤት ሊያስገቡት፡ እሰኪያቅታቸው ድረሰ... ሳንባዎቹ፡ ወይም የሆነ ነገር፡ እጅግ ተጎድተው ነበር። በጣም፡ በጣም መጥፎ ሁኔታ ላይ ነበረ። እንዲህም ተባለ፡ ከመልእክቱ በኋላ ወዲያውኑ መንፈሰ ቅዱስ፡ ለዚያ ትንሽ ልጅ ተናገረው፡ ጠራውም፡ ሁኔታውንና የመሳሰሉትን ነገሮች ነገረው፡ መፈወሱንም አወጀ።

በዚህ ሳምንትም ሄደ፡ እናቱ ወይም ወላጆቹ፡ ወይም ማንም ይሁን ብቻ፡ ወደ ሐኪሙ መልሰው ወሰዱት፡ ሐኪሙም አዲስ ሳንባዎች ተገጥመውለታል አለ፡ አያችሁ፡ አዲስ ሳንባዎች። እንደተረዳሁት ከሆነ፡ ወ—ወላጆቹ ወይም ሌላ ሰው የረጅም ርቀት ስልክ ደውለው፡ ወይም በሆነ መንገድ፡ ለጉባኤው እንዲታወቅ አድርገዋል። አያችሁ? አሁን፡ ፈጣሪ የሆነው፡ እግዚአብሔር፡ አዲስ ሳንባዎችን መፍጠር ይችላል።

32 ከ—ከጌታ ኢየሱስ ዘመን ጀምሮ ም—ምድርን ካጋጠሟት እጅግ ታላላቅ ነገሮች መካከል በአንዱ አፋፍ ላይ እንዳለን በእውነት አምናለሁ። አያችሁ? አያችሁ? ነገር ግን አሁን ልንታወቅ የምንችለው እንደ... እጅግ ትሁት ይሆናል። አያችሁ? አያችሁ፡ ሰው **ታላቅ** የሚለውን፡ እግዚአብሔር “ርኩሰት” ይለዋል። ነገር ግን ሰው **ሞኝነት** የሚለውን፡ እግዚአብሔር “ታላቅ” ይለዋል። አያችሁ? ስለዚህ አሁን ተመልከቱት፡ አያችሁ፡ እጅግ ትሁት ከመሆኑ የተነሳ... እርሱን ለመመርመር ምልክቱ በዚያ ከሌላችሁ ያመልጣችኋል፡ አያችሁ። አያችሁ?

33 አንድ ነቢይ ከምድረ በዳ ሲወጣ ተራሮች እንደ ትናንሽ አውራ በጎች እንደሚዘልሉ፡ ቅጠሎችም እጆቻቸውን እንደሚያጨበጭቡ፡ ማን አሰቦ ያውቃል፥ ያ በኢሳይያስ፡ ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ... ወይም ከሰባት መቶ አስራ ሁለት ዓመታት በፊት የተነገረ ነበረ። ፊቱ ሁሉ በጺም ተሸፍኖ፡ ትከሻው ላይም የበግ ቆዳ ለብሶ፡ የሚሰብክበት መድረክ እንኳ ሳይኖረው፡ ከአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተባርሮ፡ በዮርዳኖስ ዳርቻ ቆሞ፡ “ንስሐ ግቡ፡” እያለ ሲጮህ! ህዝቡንም “እፉኝቶች፡” እባቦች ብሎ ጠራቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ያለው ይህንን ነበረ፡ እርሱ ሲመጣ፡ “ተራሮች እንደ ትናንሽ አውራ በጎች ይዘልላሉ።” አያችሁ? ትሁታንም አይተውት ተደሰቱ።

34 አዳኝ ሆኖ እንደሚመጣ... የመጽሐፉ መጀመሪያ ከሆነው፡ ከዘፍጥረት ጀምሮ ትንቢት የተነገረለት፡ ያ ታላቅ መሲህ፡ እርሱ መሆኑን፡ እንዴት ሊረዱ ቻሉ? መሰዋዕቶች ሁሉ፡ ነቢያትም ሁሉ፡ ሁሉም ነገር ወደ እርሱ አመልክተው ነበረ። ከዚያም እርሱ ሲመጣ፡ ዲቃላ ሆኖ እንደተወለደ ተገመተ፥ አባቱ እንኳ እናቱን እንዳላገባት፡ ተገመተ። አያችሁ? ያቺም ሴት ገና ሳይጋቡ ልጁን ጸንሳ ተገኘች። በእንዲህ ዓይነት መንገድ መጣ፡ የተወለደውም በ—በአንድ ትንሽ... መልካም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ በረት ይላል። ነገር ግን በዚያን ዘመን በረት ማለት ከግድግዳ ጋ—ጋርባ ያለ ዋሻ ነበረ። አንድ ጊዜ በአሪዞና ውስጥ ለአደን ወጥቼ፡ እንደዚህ ያለ ቦታ አጋጥሞኝ ነበረ። ከዓለቶች ስንጥቅ ስር በስተጀርባ በረት ነበረ። ኢየሱስ የተወለደውም በዚህ መንገድ ነበረ፡ በዚህ ትንሽ የዓለት ስንጥቅ በረት ውስጥ በሳርና-ገለባ በተሞላ ግርግም ላይ፡ በላሞች በረት ውስጥ፡ አያችሁ፡ ከብቶች በነበሩበት ሰፍራ ነበር።

35 የአናጺ ረዳትም ሆኖ አደገ፡ ታዲያ ያ እንዴት ታላቁ ይሖዋ ሊሆን ይችላል? ነገር ግን እርሱ ነበረ፡ አያችሁ። እርሱ ነበረ። አያችሁ? በጣም ለየት ያለ ዓይነት ሰው ነበረ። ነገር ግን፡ ኦህ፡ ገና ልጅ ሳለ፡ ያንን ቃል በማወቅ ካህናቱን አስገረማቸው። ምክንያቱም ምንድነው? እርሱ ቃል ነበረ። አያችሁ? እርሱ ቃል ነበረ።

ምንም መጽሐፍ አልጻፈም። አንድም—አንድም ቃል አልጻፈም። የጻፈው ብቸኛው ቃል፡ አንዲት ሴት በምንዝር በተያዘች ጊዜ፡ በ—በአሸዋ ላይ

የጻፈውና፡ መልሶ ያጠፋው፡ ይመስለኛል። አንድም ቃል አልጻፈም። ለምን? እርሱ ቃል ነበረ። አያችሁ? እርሱ ቃል ነበረ። መጻፍ አላስፈለገውም፥ ሕይወቱ ኖሮታልና። እርሱ ቃል ነበረ። እርሱ... "የአባቴን ስራ ባላደርግ፡ አትመኑኝ።" አያችሁ? "ቃሉ አደርገዋለሁ ያለውን ነገር በትክክል ባላደርግ፡ ቃል አይደለሁም። ዳሩ ግን ካደረግሁ... " ማለት የፈለገው ያንን ነበረ። እርሱ ቃል ነው።

36 ስለዚህ አሁን ለ—ለሚመጣው የፈውስ አገልግሎትና ለጌታ እራት ራሳችሁን አዘጋጁ። ከቻላችሁ ከእኛ ጋር ብትቆዩ ደስ ይለናል። ካልቻላችሁ፡ ወዲያውኑ ስንብት እናደርጋለን።

37 ደግሞም ይህንን አትርሱ፡ ጸልዩልኝ፡ በዓለም ሁሉ ካሉ እጅግ በጣም ጣፋጭ ለሆነችው ለባለቤቴም ጸልዩ፥ ለ—ለልጆቼም ጭምር። አሁንም እያንዳንዳቸውን፡ ለጌታ ለኢየሱስ፡ አሳልፌ ሰጥቻቸዋለሁ።

38 አሁን፡ ቤኪ ልክ እንደ ትንሿ ሪኬታ በምትሆነው የዕድሜ ክልል ውስጥ ናት፡ ታውቃላችሁ፡ እንዲህ ብለን እንደምንጠራው፡ ልክ እ—እንደ ትንሽ አፍላ-ወጣት ነች። አሁን ልክ በዚያ የዕድሜ ክልል ውስጥ ናት። ዳሩ ግን፡ አሁን፡ በጣም ጣፋጭ ልጅ ናት፡ ስለዚህም ጌ—ጌታን አመሰግናለሁ፥ ማጨስ የለም፡ መጠጣት የለም፡ መንከራተት የለም፡ ምንም የለም። ነገር ግን ልክ በዚያ የዕድሜ ክልል ውስጥ ስላለች፡ ግ—ግድየለሽ ናት። ቤተክርስቲያን መሄድ አትፈልግም፡ ከሄደችም፡ እዚያ ኋላ ላይ ተቀምጣ፡ ማስቲካ ታኝካለች፡ ተነስታም ትወጣለች። ያ ነው፡ አያችሁ። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ማየት እፈልጋለሁ።

39 ጆሴፍን ላየው እፈልጋለሁ፡ ያንን ልጅ... አንድ ቀን ወደ መድረክ መራመድ በማልችልበት ጊዜ፡ ይህንን ያረጀ-የተቀደደ መጽሐፍ ቅዱስ ወስጄ ለእርሱ ልሰጠውና፡ "ጆሴፍ፡ ልጄ፡ ከእርሱ ጋር ጽና፡" ልለው እፈልጋለሁ። ከዚያም ወደ ላይ ለመውጣት ዝግጁ እሆናለሁ። በአንድ ሰፍራ ንፋስ ሲነፍስ ልሰማ፡ ወደ ላይ ልመለከት፡ እጄን ላወዛውዝና፡ ልነሳ እፈልጋለሁ።

እንጸልይ።

40 አባት አምላክ ሆይ፡ ህይወታችን በሙሉ በዚያ ውስጥ ተጠቅልሏል፡ እሱም አንተ ነህና፡ አንተም ህይወታችን ነህ። አሁን እዚህ፡ ጌታ ሆይ፡ ይ—ይህንን የተናገርኩትን ምልክት በእጃቸው የያዙ አንዳንዶች አሉ። ያንን ምልክት የራሳቸው አድርገዋል፡ ነገር ግን አሁንም ታመዋል። ዛሬ ማታ ላበረታታቸው፡ ያ—ያንን ከእግዚአብሔር-የተሰጣቸውን መብት እንዲወስዱ ላበረታታቸው እፈልጋለሁ። ያንን ዲያብሎስ የማሸነፍ መብት አላቸው። እርሱ አስቀድሞ ተሸንፏል፡ ዝም ብሎ እያስፈራራቸው ብቻ ነው። ለእነርሱም እጠይቅሃለሁ፡ አባት ሆይ።

41 አሁን ቃሉን እንድናገር እርዳኝ። ጌታ ሆይ፡ እዚህ በጻፍኳቸው ጥቂት ማስታወሻዎች፡ በጻፍኳቸውም ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት፡ በእኔ በኩል ተናገር። ጌታ ሆይ፡ እንድትረዳኝ፡ ወደ ቃሉ ገብቼ ለእግዚአብሔር ክብር እምነትን እንድትሰጣቸው እጸልያለሁ። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ። አሜን።

42 ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ አሁን በፍጥነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ ኤርምያስ መጽሐፍ፡ ወደ 29ኛው ምዕራፍ እንድትገልጡ እፈልጋለሁ። ወይም፡ ካልፈለጋችሁ፡ ዝም ብላችሁ ምልክት አድርጉበት። ኤርምያስ፡ 29ኛው

ምዕራፍ። ከኤርምያስ 10ኛው ቁጥር፡ ከ29ኛው ምዕራፍ 10ኛው ቁጥር እንጀምራለን። እንዲሁም፡ ከሉቃስ፡ 16ኛው ምዕራፍ፡ ከ14ኛው ቁጥር ጀምረን እናነባለን።

43 አሁን እ—እ—እየገለጣችሁ ሳለ፡ ርዕሴን እነግራችኋለሁ። የዛሬ ማታ ርዕሴ **መጣበቦች** የሚል ነው። እኔም... መጣበብ፡ አሁንም፡ መጣበብ ምን እንደሆነ፡ ታውቃላችሁ።

አሁንም ከኤርምያስ 29ኛው ምዕራፍ፡ 10ኛው ቁጥር እናነባለን።

**ጌታ እንዲህ ይላልና፡ ሰባው ዓመት በባቢሎን በተፈጸመ ጊዜ እጐበኛችኋለሁ፡ ወደዚህም ስፍራ እመልሳችሁ ዘንድ፡ መልካሚቱን ቃሌን እፈጽምላችኋለሁ።**

**ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ይላል ጌታ**... (ደስ አይልም ወይ?)... **ፍጻሜና ተስፋ፡** እሰጣችሁ **ዘንድ፡ የሰላም አሳብ ነው እንጂ፡ የክፉ ነገር አይደለም።**

**እናንተም ትጠሩኛላችሁ፡ ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፡ እኔም እሰማችኋለሁ።**

**እናንተ ትሹኛላችሁ፡ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ፡ ታገኙኛላችሁ።**

**ከእናንተም ዘንድ እገኛለሁ፡ ይላል ጌታ፥ ምርኮአችሁንም እመልሳለሁ፡ ከአሕዛብም ሁሉ ዘንድ... እናንተንም** ካሳደድሁ**በት፡ ስፍራ ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፡ ይላል ጌታ፥ እናም... እናንተንም** ለ—**ለምርኮ ወዳፈለስሁበት ስፍራ እመልሳችኋለሁ፡** ወደ ጴንጤቆስጤ እመልሳችኋለሁ!

ያንን፡ ራሴ ነኝ ያስገባሁት። እንደዚያ አይልም። ያንን ለቤተክርስቲያን ነው ያልኩት።

ሉቃስ 16፡ ከ15ኛው ቁጥር፡ ወይም ከ16ኛው ቁጥር ጀምሮ እናነባለን።

**ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ነበሩ፥ ከዚያ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፡ ሁሉም ወደ እርሰዋ** በኃይል **ይገቡባታል።**

"ሁሉም ወደ እርሰዋ በኃይል ይገቡባታል።" በቀላሉ፡ ዝም ብሎ ወደ እርሷ አይራመድም፡ ነገር ግን በኃይል መግባት አለበት። አያችሁ? አሁን፡ "በፍጹም ልባችሁ ስትፈልጉኝ፡ ያን ጊዜ እገኛለሁ።"

44 ከነዚያ ሰባ ዓመታት በኋላም፡ በምድር ሁሉ ላይ ከተበተኑበት ሕዝቡን እንደሚመልሰና፡ ወደ ወጡበት ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚያመጣቸው፡ ተስፋ ሰጠ፥ ልክ በዚያው መንገድ አደረገው። በትክክል።

45 አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች ስ—ስለ **መጣበቦች** እንነጋገራለን። አብዛኛውን ጊዜ፡ ወደ መጣበብ ውስጥ እንድንገባ የሚያደርገን፡ አጣዳፊ ሁኔታ ነው። አያችሁ? ይህ መሆኑ ያሳዝናል፡ ዳሩ ግን የሰው ልጆች በአዕምሯቸው እጅግ ቸልተኞች ከመሆናቸው የተነሳ፡ አጣዳፊ ሁኔታን ይጠይቃል። የሆነ ነገር ይነሳል፡ ከዚያም ሲነሳ፡ ያ—ያ ወደዚያ መጣበብ ውስጥ ይከታቸዋል። በእውነቱም፡

ያንን በመጣበብ ውስጥ ማድረጋቸው፡ ያንን እውነተኛ ማንነታችሁን አውጥቶ ያሳያል። በመጣበብ ጊዜ ውስጥ፡ ከምን እንደተሰራችሁ ያሳያል። አብዛኛውን ጊዜ በውስጣችሁ ያሉትን መልካም ነገሮች ሁሉ አውጥቶ ያሳያል።

46 ሰዎች ሞት አፋፍ ላይ ሲደርሱና፡ እንደሚሞቱ ሲያውቁ፡ በሕይወታቸው ሙሉ፡ በምስጢር ደብቀዋቸው የነበሩትን ነገሮች፡ በመጣበብ ሰሜት ውስጥ ሆነው፡ ሊናዘዙ ሲሞክሩ ሰምቻለሁ። አያችሁ? በዚያ መጣበብ ውስጥ ሆነው፡ "**ይህንን** ውሰድና አስተካክለው፡ ሂድ፡ እባክህ፥ ሂድ፡ ይህንን አድርግ፡" ለማለት ይሞክራሉ፡ አያችሁ። ያንን አስቀድመው ማድረግ ነበረባቸው፡ አያችሁ፡ አጣዳፊ ጊዜ እስኪመጣ መጠበቅ አልነበረባቸውም። "**እንዲህ-እና-እንዲያ** ታደርግልኛለህ?" አጣዳፊ ሁነታ መጣበብን ያስከትላል። ይህም፡ አስጨናቂው ጊዜ ከመምጣቱ በፊት ማድረግ ነበረብን።

47 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ የፋሲካን ምልክቶች እየወሰድን እንደሆነ እንገነዘባለን። ፋሲካ የተወሰደው በአስጨናቂ ጊዜ ውስጥ፡ በመጣበብ ጊዜ ውስጥ ነበረ። አስተውላችኋል በ—በዘፀአት 12ኛ ምዕራፍና፡ በ12ኛው ምዕራፍ 11ኛው ቁጥር ላይ፡ ይመስለኛል፡ እንዲህ ይላል፡ "ይህንን ፋሲካ ወገባቸውን ታጥቃችሁ፡ ጫማችሁን አድርጋችሁ፡ በትራችሁንም በእጃችሁ ይዛችሁ ብሉት፡" አያችሁ፡ ተጣባችሁ ትበሉታላችሁ።

48 ታላቁን የእግዚአብሔርን እጅ አይተው ነበረ። ተአምራቱን ሁሉ አይተው ነበረ፡ ከዚያም በምልክቱ ስር መጥተው ነበረ። ከምልክቱም ስር በነበሩበት ጊዜ፡ የጌታን እራት በ—በመጣበብ ውስጥ ወሰደው ነበረ፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር በፍርድ ሊመታ እንደተዘጋጀ ያውቁ ነበርና።

49 የሚያናውጥ ጊዜ ነበረ። የነቢዩ ቃል አንድም ጊዜ አልወደቀም ነበርና፡ እያንዳንዱ ሰው ራሱን የሚመረምርበት ጊዜ ነበረ። እውነት መሆኑ ተረጋግጦ ነበረ። የተናገረው ማንኛውም ነገር፡ ልክ እርሱ በተናገረው መንገድ በትክክል ተፈጽሟል። የእሳቱ ዓምድ አሁንም በዚያ ነበረ። ከዚያም፡ እግዚአብሔር የሚያልፈው በበሩ ላይ ምልክቱን ሲያይ ብቻ እንደሆነ፡ ነቢዩ አሳውቆ ነበረ። መጣበብ ነበረ።

50 እነዚያ ልጆችም እንደሚመስለኝ... እነዚያን ትልልቅ ጥቁር ክንፎች፡ ከሰማይ እንደ ጢስ፡ ወደ ከተማዋ ሲወርዱ ባዩ ጊዜ፡ ከየቤቱ የሚወጣውን ጩኸት ሲሰሙ፡ ልጆቹ ወደ አባታቸው ሄደው እንዲህ ሳይሉ አይቀሩም፡ "አባዬ፡ ምልክቱ ስር መሆናችንን እርግጠኛ ነህ?"

እርሱም ወደ በሩ ሄዶ፡ መቃኑን፡ ጉበኑን ተመልክቶ፡ እንዲህ ይላል፡ "ልጄ፡ ይህ እንደ ቃሉ ነው።"

"እኔ የበኩር ልጅህ ነኝ፡ ልብ በል። አባዬ፡ እርግጠኛ ነህ?"

51 "እርግጠኛ ነኝ! ነቢዩ እንደነገረን ነው፡ እርሱም የጌታ ቃል አለው። እንዲህ አለ፡ 'ደሙን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ። ለአንድ ቤት አንድ በግ ውሰዱ፡' ብሏል። ልጆች ሁላችሁ እስገብቻለሁ። አንተ ታላቅ ልጄ ነህ፡ ዳሩ ግን የበኩር ልጄ ነህ። እዚያ ውጭ እየሞተ ያለው በኩር ነው፥ ነገር ግን ደሙ **ይኸው**። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ያለው ይህንን ነው። ስለዚህ፡ አረፍ በል፡ እግዚአብሔር ቃል ስለገባ፡ በሰላም አረፍ በል። አያችሁ?"

“እሺ፡ አባዬ፡ ለምንድነው ጫማህን ያደረግኸው? ለምንድነው በትር በእጅህ የያዝኸው? በአንደኛው እጅህ ቁራሽ ዳቦ በሌላው ደግሞ በግ የያዝኸው ለምንድነው? መራራ እፅዋትንና ሌሎችን ነገሮች የያዝኸው ለምንድነው? ለምንድነው የምትበላው? ፊትህ ላይ ላብ የሚንጠባጠበውስ ለምንድነው?”

“ልጄ፡ ሞት ሊመታ ነውና።” አያችሁ፡ ይህ በመጣበብ ጊዜ ውስጥ ነበረ።

52 አሁን፡ እየኖርን ያለንበት ዘመን... ወይም፡ በሌላ አነጋገር፡ እየኖርንበት ያለው ዘመን ቤተክርስቲያንን ሙሉ በሙሉ ወደ መጣበብ ውስጥ ሊከታት ይገባል ብዬ አምናለሁ። ዛሬ ጠዋት ከእግዚአብሔር እንጂ፡ ከእኔ ያልሆነውን፡ መልእክት ከሰማንበት ጊዜ ጀምሮ፡ በበቂ ሁኔታ ስለተጫወትን፡ ይህ መላው ጉባኤ ወደ መጣበብ ውስጥ ሊገባ ይገባል ብዬ አምናለሁ። በበቂ ሁኔታ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደናል። አንድ ነገር ማድረግ አለብን።

53 እንዴት ነው በሌሎች ላይ ታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች ሲደረጉ እያየን የምንቀመጠው፡ እኛስ? በእግዚአብሔር ፊት፡ ቆርጠን እንድንነሳ፡ የመጣበብ ሁኔታ ሊፈጥርብን ይገባል። ከቃሉ እንዳነበብነው፡ የእርሱ መምጣት ምልክቶች ይህንን መላ ጉባኤ... መንፈስ ቅዱስ፡ “ወደ አንድ የተወሰነ ቦታ ሂዱ፡ **ይህ-እና-ያ** ነገር ይሆናል” ብሎ ነግሮናል፡ ምን እንደሆነ አልነገረንም፡ ምን እንደሚሆን ግን ነግሮናል። ወደዚያ እንሄዳለን፡ ልክ በዚያው መንገድ ይሆናል። ጋዜጦች ያወጡታል፡ መጽሔቶች ያወጡታል፡ ሰዕሉንም ያሳያሉ። ወደዚህ ተመልሰን ስንመጣና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደብቀው የነበሩት፡ እነዚያ ታላላቅ ሚስጥሮች፡ ከዚህ በፊት አውቀነው፡ በማናውቀው አዲስ መስክ ላይ ሲከፈቱልን፡ እንዲሁም ከጌታ ኢየሱስ መምጣት ጋር ፍጹም ሆኖ ሲዋሃድ እናያለን።

54 ከዚያም፡ በመልእክቶቹ መጨረሻ ላይ፡ የታላቁን መንፈስ ቅዱስ አሰራር ተመልከቱ፡ በሰዎች ፊት በሚታይ ሁኔታ ሲወርድ እዩት፡ ፎቶግራፉ እንኳ ሲነሳ ተመልከቱ። ሲሰራና ሲያሳይ እዩት ሰው እንዳልሆነ፡ ዝም ብሎ ሰባኪ እንዳልሆነ፡ የሆነ አይነት ጉባኤ እንዳልሆነ ያሳያል። የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ውስጥ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አሁንም እያሳየ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው። አሁን በሙሽራይቱ አካል ውስጥ ተገልጧል። ይህ ወደ መጣበብ ሊከተን ይገባል።

55 እነዚያ ሰዎች የእግዚአብሔርን እጅ አይተው ነበረ። በዚያች በፋሲካ ምሽት፡ በመጣበብ... ወሰዱት፡ ምክንያቱም አንድ ነገር ሊሆን እንደሆነ አውቀው ነበረና። እኛም አንድ ነገር ሊሆን እንዳለ እናውቃለን። ደግሞም አስታውሱ፡ የጌታ መምጣት ድንገተኛና፡ ሚስጥራዊ መሄድ ይሆናል። በሌሊት እንደሚመጣ ሌባ መጥቶ ይወስዳታል። አሰቡት እስቲ፡ በድንገት፡ ከቤተሰባችን አባላት መካከል የተወሰኑት ሄደው፡ ወደ ኋላ ብትቀሩ! በእግዚአብሔር ጸጋ፡ ወደ ኋላ እንዳንቀር፡ ይህ፡ ወደ መጣበብ ሊከተን ይገባል። “የማልፈልገው አንድ ነገር ቢኖር... ጌታ ሆይ፡ አትተወኝ፡ አትተወኝ።”

56 ከጥቂት ቀናት በፊት ሜል ጆንሰን ያንን መዝሙር ሲዘምር እየሰማሁት ነበረ፥

እምባዬ ወደ ታች ሲፈስ አሰበኝ፡ አዎ

ወዳጆች በአጠገቤ በማይኖሩበት ጊዜ አሰበኝ
ይህንን የዮርዳኖስን ወንዝ ስሻገር
ስም ስትጠራ፡ እኔን አስበኝ።

57 ስሜ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ፡ እንዲጻፍ እፈልጋለሁ። ስም ሲጠራ እርሱ እንዲያስበኝ እፈልጋለሁ። ያም ወደ መጣበብ ይከተኛል፡ ያም፡ ጳውሎስ እንዳለው፡ “ወንጌልን ከሰበክሁ በኋላ እኔ ራሴ የ—የተገለልኩ፡ የ—የተጣልሁ እሆን ይሆን?” ሊሆን ይችላል። ስለዚህ፡ ከእነዚህ ሁሉ የሰብከት ዓመታት በኋላ፡ እርሱን የማሳዝንበት ሁኔታ፡ ልደርስ እችላለሁ ብዬ ሳሰብ፡ ወደ መ—መጣበብ... የመጣበብ ደረጃ ውስጥ ይከተኛል? ቀጣዩ እርምጃ ምንድነው? ቀጥሎ ምን ማድረግ አለብኝ? ወደ መረበሽ ደረጃ ውስጥ ይከተኛል። ምን ማድረግ እችላለሁ? ወደ ተራሮችና ወደ ሸለቆዎች ውስጥ ይጥለኛል። አስቸጋሪም ነው፡ ምክንያቱም፡ ከሰዎች ጋር ስሆን፡ አንዳንዶችን ወደ ክርስቶስ አሸንፍ ዘንድ፡ ለሁሉም ሰው ሁሉንም ነገር መሆን አለብኝ፡ ዳሩ ግን ያ ምልክት ሁልጊዜ ከፊቴ አለ። አያችሁ?

58 አሁን እየመጡ ያሉትን ነገሮች አያለሁ፡ ለሰዎች ግን መናገር አትችሉም። የተለያዩ ነገሮችን ታያላችሁ፡ ነገር ግን ተከልክላችኋል። እነርሱ የሚጠይቋቸው ራእዮች፡ ብትነግሯቸው አንዳንዴ ያዝናሉ፡ እናንተም ያንን ከማድረግ የተሻለ ታውቃላችሁ። ከዚያም በራእዮች ውስጥ በጣም ርቃችሁ ስለምትሄዱ ሁሉም ነገር ራእይ ይሆንባችኋል፡ ያም ወደ መረበሽ ደረጃ ውስጥ ይከታችኋል። እ—እናንተም ትመለከቱና፡ “አሁን በራእይ ውስጥ ነኝን” ትላላችሁ? ልክ አሁን እዚህ እንደተቀመጣችሁ፡ “ይህ ራእይ ነውን? በእርግጥ የቆምኩት የት ነው?” አያችሁ፡ ራ—ራሳችሁን ከልክ በላይ ታስራላችሁ፡ ራሳችሁን ከልክ በላይ ታደክማላችሁ። እንዲሁም ስለ ሰዎች ባታውቁት የምትመኙትን ነገሮች ታውቃላችሁ። እነዚህን ነገሮች የሚመኙ ሰዎች፡ እነዚህን ነገሮች ማወቅ የሚፈልጉ፡ ያ ዓይነት አገልግሎት ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል አይገነዘቡም። ከእርሱ ጋር ምን አብሮ እንደሚሄድ አታውቁም። ከዚያም፡ “ጌታ አምላክ ሆይ፡ መልስ መስጠት እንዳለብኝ አውቃለሁ” ወደማለት መጣበብ ውስጥ ይከታችኋል።

59 ጃክ ሙር አንድ ጊዜ እንዲህ አለኝ፡ “በፍርድ ቀን አንተ መልስ መስጠት እንዳለብህ ሆኜ፡ መልስ መስጠት አልፈልግም።” እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች በእጅህ አሰቀምጧቸዋል፡ አንተም ስለ እያንዳንዳቸው መልስ ትሰጣለህ። ስለ አገልግሎትህ መልስ ትሰጣለህ” አለ። ይህ ከአሰራ አምስት ዓመት ገደማ፡ ወይም ምናልባት አሰራ ሰምንት ሆኖታል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ በመጣበብ ውስጥ ቆይቻለሁ። ምን አደርጋለሁ?

“ጌታ ሆይ፡ አንተ የምትለውን ብቻ እንድናገር አድርገኝ። እውነቱን እንድነግራቸው፡ ወይም ምንም እንዳልናገር አድርገኝ።” ይህ ወደ መጣበብ ውስጥ ይከተኛል።

60 ከዚያም እነዚህ ምልክቶች ሲመጡ ማየት፡ መንፈስ ቅዱስ እዚያ ወሰደን፡ እነዚያን ማኅተሞች አምጥቶ፡ እንደዚያ ሲያሰቀምጣቸው ማየት። የቤተክርስቲያንን ዘመናት አምጥቶ ሲያሰቀምጥ፡ ከዚያም በዚያ ታላቅ የእሳት ዓምድ ውስጥ ወርዶ፡ ራ—ራሱን ሲገልጥ ማየት። ከዚያም በቀጣዩ ነገር፡

በሰባቱ ማኅተሞች ላይ ወርዶ፡ ሲገልጠው ማየት። በጋዜጦችና በመጽሔቶች ላይ እንኳ አወጣው። ከዚያም መጥቶ የእግዚአብሔርን መላእክት መውሰድ፡ እነዚያን ሰባት መላእክት ከሰባት መልእክቶች ጋር ወሰዳቸው፡ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን በትክክል አረጋገጠው። ከዚያም፡ በዚያን ጊዜ፡ መጥቶ እነዚያን ማኅተሞች ማምጣት... እነዚያን ምልክቶች፡ የፍጻሜውን ዘመን ብልጭታዎች፡ ወደ ሰዎቹም አምጥቶ ምን እንደሆኑና፡ ስለ እርሱም ሁሉ መንገር፡ ጌታም ልክ በዚያው ሰፍራ እየሰራ ራሱን በቦታው እንዳለ ማሳየቱ በመጣበብ ውስጥ ይከተኛል። ከዚያም፡ ልክ እንደ ዛሬ ጧት፡ መጥቶ ያንን ምልክት ከእያንዳንዱ ሰው ላይ መፈለጉ። ከዚያ፡ እናንተ ህዝቦቼ ናችሁ። የምወዳችሁ እናንተ ናችሁ፡ እነዚህና እነዚያ ቴፖቹን የሚያዳምጡና፡ የመሳሰሉት ናቸው። ታዲያ ይህ በምን ዓይነት መጣበብ ውስጥ እንደሚከተኝ አያችሁ።

61 መጣበብ። የእርሱ መምጣት ምልክቶች እያንዳንዱን የክርስቶስ አካል ወደ መጣበብ፡ ስለ ነፍሳችን፡ ስ—ስ—ስለ ወደፊቱ ደህንነታችን መጣበብ ውስጥ ሊያስገቡት ይገባል። እንግዲህ፡ ዓለሙን ሁሉ ብናተርፍ ምን ልንሆን ነው? ምንድን ነን፡ የምንኖረውስ ለምንድን ነው? የምትሰሩትስ ለምንድን ነው? የምትበሉትስ ለምንድን ነው? የምትታገሉትስ ለምንድን ነው? ለመኖር። የምትኖሩት ለምንድን ነው? ለመሞት። ለመሞት ብቁ እስካልሆናችሁ ድረስ ለመኖርም ብቁ አይደላችሁም። እውነት ነው።

62 ብዙ የፈውስ ተአምራትን እናያለን፡ ይህ ወደ መጣበብ ውስጥ ሊያስገባን ይገባል።

63 ያ ትንሽ ልጅ... አሁን ሚስ ፔኪንፓውን እያየኋት ነው? ይህች ሚስ ፔኪንፓው ናት? እዚህ ልጁን፡ ወይስ ሌላ ነገር ይዘሽ የነበርሽው አንቺ ነሽ? ለምን፡ ስለ እርሰዋ ስናገር የነበረችው ሴት እዚሁ ተቀምጣለች። ዞር ብዬ ስመለከት አየኋት።

64 አሁን እግዚአብሔር ለዚያ ትንሽ ልጅ ያንን ማድረግ ከቻለ፡ ይህ እናንተን ወደ መጣበብ ውስጥ ሊያስገባችሁ ይገባል።

65 ከኒው አልባኒ የመጣ አንድ ሰው፡ ዛሬ ማታ እዚህ ሊኖር ይችላል። የወንድሜ የሮበርሰን ጓደኛ ነው። እዚህ አንድ ትንሽ ልጅ ነበረው። ሚስቱ በአንድ ወቅት የካንሰር ህመም ነበረባትና ተፈውሳለች ብዬ አስባለሁ። እሁ—አሁንም፡ ትንሹ ልጅ በጣም የከፋ አስም ይዞት በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ ይገኛል። ትንሹ ልጅ፡ ራሱ፡ ጉሮሮው ላይ ካንሰር ሊሆን የቀረበ ደረጃ ላይ ደርሷል። አያችሁ? ከዚያም ትንሹን ልጅ አመጣው፡ እዎ፡ እዚያ ኋላ፡ እጁን ወደ ላይ አውጥቶ አያለሁ፡ ዛሬ ጠዋት ተጸልዮለት ነበር፡ አያችሁ።

66 መጣበብ! ሚስቱ በካንሰር ልትሞት ስትል፡ እግዚአብሔር ሊፈውሳት እንደሚችል አውቆ ነበር። እግዚአብሔር ሚስቱን መፈወስ ከቻለ፡ እግዚአብሔር ልጁንም መፈወስ ይችላል። ይህም ወደ መጣበብ ሁኔታ ውስጥ ይከተዋል። አያችሁ? መምጣት አለባችሁ፥ በምትጣበቡበት ጊዜም፡ እግዚአብሔር ይሰማችኋል። ነገር ግን ዳተኞች ከሆናችሁና፡ ቢያደርገውም ባያደርገውም ግድ የማይሰጣችሁ ከሆነ፡ እንግዲህ፡ ያ የተለየ ነው። ግድ ይለኛል ትሉ ይሆናል፡ ነገር ግን ይህ እንዲሆን መጣበብን ይጠይቃል።

67 መጣበብ የሌለበት ምክንያት የፍቅር እጥረት ስለሆነ ነው ብዬ አምናለሁ፡ የእግዚአብሔር፡ የእግዚአብሔር ፍቅር እጥረት። የእግዚአብሔር ፍቅር መጣበብን ያመጣል ብዬ አስባለሁ። እግዚአብሔር በውስጣችሁ ካለ፡ ምልክቱ በውስጣችሁ ካለ፡ እንዲሁም የጊዜያቱን ሁኔታዎች ስታዩ፡ ሰዎችም አሁን ባሉበት መንገድ በኃጢአት ውስጥ ሲዘፈቁ ስታዩ፡ ወደ መጣበብ ውስጥ ያስገባችኋል። እንደሚያስገባችሁ አምናለሁ።

68 ይህን መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ ቃሉ፡ በገላትያ 5፥6 ላይ፡ "እምነት በፍቅር ይሰራል" በማለት፡ በግልጽ ያስቀምጠዋል። አያችሁ? "እምነት በፍቅር ይሰራል።" እምነት ሊኖራችሁ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ፡ መጀመሪያ ፍቅር ሲኖራችሁ ነው። ምክንያቱም፡ ደግሞም፡ እምነት የፍቅር መነሳሻ ነው። መነሳሻ፡ እ—እምነት ማለት ልክ ይኸው ነው። የፍቅር ማነቃቂያ ነው። አሁን፡ እናንተ፡ ፍቅር ከሌላችሁ፡ እምነት ሊኖራችሁ አይችልም። አያችሁ?

69 ሚስታችሁን የማትወዷት ከሆነ በእርስዋ ላይ እምነት ሊኖራችሁ እንዴት ይችላል? ያ **በፊሊዮ** ነው። ታዲያ **በአጋፔ**፡ ለእግዚአብሔር ሲሆንስ? እግዚአብሔርን የማትወዱት ከሆነ እንዴት ሊሆን ይችላል?

ሚስታችሁን እንደምትወዷት ብትናገሩ፡ ስለ ፍቅራችሁ ግን ነግራችኋት የማታውቁ ከሆነ፡ አብራችኋት ተቀምጣችሁ ፍቅራችሁን የማታሳዩአት ከሆነ፡ የማትገልጹላት ከሆነ፡ የማትስሟት፡ የማታቅፏት ከሆነ፡ እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ ምርጥ ምግብ አብሳይ እንደሆነች፡ የምታውቁትን ሁሉ፡ ምን ያህል ቆንጆ እንደሆነች፡ ምን ያህል እንደምትወዷት የማትነግሯት ከሆነ፥ ይህን የማታደርጉ ከሆነ፡ እርስዋ መቼም አታውቀውም። ነገሩ እንደዚህ ነው። የምትወዷት ከሆነ፡ ትገልጹላታላችሁ።

70 ለእግዚአብሔርም የምናደርገው እንደዚሁ ነው። ስንወደው፡ ስለሱ እንነግረዋለን። ተቀምጠን እናደንቀዋለን፡ እናመልከዋለንም። ደግሞም፡ አያችሁ፡ ፍቅር ወደዚህ ይመራናል።

71 አሁን ለሚስታችሁ መደረግ ያለበት ነገር ቢኖር ምን ይሆናል? ለምን፡ ያንን ለማድረግ ወደ መጣበብ ውስጥ ያስገባችኋል። አንድ ሰው ሚስታችሁ ካንሰር ይዟታል ቢላችሁስ? አንድ ሰው ሚ—ሚስታችሁ ቲቢ ይዟታል፡ ልትሞትም ነው ቢላችሁስ? ሆኖም፡ እናንተ፡ እ—እናንተ ማንኛውንም ነገር ታደርጋላችሁ። አያችሁ፡ ወደ መጣበብ ውስጥ ያስገባችኋል።

72 ነገሩም ያው ነው። እምነት ሊኖረን ከመቻሉ በፊት ፍቅር ሊኖረን ይገባል። እምነት ደግሞ... እውነተኛ ፍቅር ሲኖረን፡ ምን ያደርጋል? ለእግዚአብሔር እምነታችንን ወደ ጦር ግንባር ይገፋዋል። አያችሁ? ለእግዚአብሔር ለቃሉና ለህዝቡ ያለው እውነተኛ አምላካዊ ፍቅር፡ እምነትን ወደዚያ ይገፋዋል። ፍቅር እምነትን ይይዘውና፡ በቃ፡ "ና፡ እንሂድ" ይለዋል! ይወጣልም፡ ምክንያቱም ፍቅር የሚያደርገው ይህንኑ ነውና።

73 ዮሐንስ 14፥23 ላይ፡ ኢየሱስ፡ "የሚወደኝ ቢኖር፡ ቃሌን ይጠብቃል" አለ። አሁን በተናገረው ነገር ላይ እምነት ሳይኖራችሁ ቃሉን መጠበቅ አትችሉም። ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እግዚአብሔርን የሚወድ ከሆነ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይጠብቃል። "የምፈውስህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፡" ካለ፡ ያንን ያምናል። ፍቅር ሁሉን ስለሚቆጣጠር፡ ፍቅር እንዲያምን ያደርገዋል። "በሰዎችና በመላእክት

ልሳን ብናገር፡ ፍቅር ግን ከሌለኝ፡ ከንቱ ነኝ፡ አያችሁ። ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ቢኖረኝ፡ ፍቅር ግን ከሌለኝ፡ ከንቱ ነኝ።" እግዚአብሔር ፍቅር፡ የፍቅር አምላክ ስለሆነ፡ ፍቅር ሁሉን ያሸንፋል። አሁን፡ አዎ፡ ወዳጄ! ኢየሱስ፡ "የሚወደኝ ቢኖር፡ ቃሌን ይጠብቃል" ብሏልና።

74 እግዚአብሔር የተጣበበች ነፍስን እንደሚያገኝ እውነት መሆኑን እናውቃለን። አሁን፡ ሁላችንም ያንን እናውቃለን። ሆኖም ወደዚያ፡ ወደዚያ ጭንቀት፡ ወደ መጣበብ ውስጥ ሊያስገባን አብዛኛውን ጊዜ አንድ ነገር ያስፈልገናል። ያንን ለማድረግ አንድ ነገር ይጠይቃል።

75 በያዕቆብ 5፥15 ላይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንዲህ ይላል፡ ይህም፡ "የማትበገር የቅንዓት" ይህም መጣበብ ነው፡ "የማትበገር የጻድቅ ሰው የቅንዓት ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። ጻድቅ ሰው፡ ጥሩ ሰው፡ በምጥ ውስጥ ሲሆን፡" ወይም የነፍስ ጉዞ፡ ወይም ምጥ፡ አንዳቸውም ቢሆኑ ኃይል ታደርጋለች። "ትራቭል" የ—የተሻለ ቃል ነው ብዬ እሰባለሁ። ትራቬል፡ ወይም ትራቭል፡ የፈለጋችሁትን መጥራት ትችላላችሁ። ነገር ግን እ—እ—አንዲት ነፍስ ወ—ወደ መጣበብ፡ ወደ ምጥ ውስጥ ስትገባ፡ ምልክቱን ሊያሳይ የሚችል የማትበገር የቅንዓት ሰው ጸሎት፡ የሆነ ነገር ታደርጋለች። አያችሁ?

76 እዚህም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በያዕቆብ 16፡ 5፥16 ላይ፡ የተናገረውን አስተውሉ፡ እንዲህ ይላል፡ እ... "ኃጢአታችሁን ተናዘዙ፡" ትክክል ሁኑ፡ ለዚህ በመዘጋጀት፡ "እርስ በርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ።" ም—ምንም ጥፋት ሳይኖራችሁ... ሰዎች እንዲጸልዩላችሁ ጠይቁ፡ እርስ በርሳችን ኃጢአታችንን እየተናዘዝን፡ አንዱ ለሌላው መጸለይ አለበት። ይኸውና፡ በፍቅር፡ ፍቅር፡ ስህተቴን ለእናንተ መናዘዝ እንደምችል እርግጠኛ ነኝ፥ እናንተም ስህተታችሁን ለእኔ መናዘዝ ትችላላችሁ። እኔም እጸልይላችኋለሁ፡ እናንተም ትጸልዩልኛላችሁ ብዬ እስካሰብ ድረስ እወዳችኋለሁ፥ እንዲሁም እስኪመለስልን ድረስ፡ የማትበገር የቅንዓት ጸሎት፡ ከእርሱ ጋር እንቆያለን። ይህ፡ ይህ መጣበብ ነው። ይህ ሁልጊዜ ሊኖረን የሚገባው ነገር ነው።

77 ስለዚያ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን እንውሰድ፡ ምን እንደተፈጠረ፡ አሁን፡ ለሌላ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ለአስራ አምስት ደቂቃዎች ያህል እንመልከት።

78 ያዕቆብ፡ ጎርምሶ ነበር፡ መጀመሪያ ትንሽ... ዓይነት ግድ የለሽ ልጅ ነበር። በራሱ አእምሮ ብኩርናው ለእሱ ሁሉን ነገር ማለት እንደሆነ እንደሚያውቅ ይመስለው ነበር፡ እንዴት ማግኘት እንደነበረበት ግድ አልነበረውም፡ ዋናው ማግኘቱ ብቻ ነበር። ካገኘውም በኋላ፡ ብኩርናውን ስላገኘ፡ ሁሉ ነገር የተስተካከለ መሰሎት ነበር። ጉዳዩ እልባት ያገኘ መሰሎት ነበር። ሜዳ ላይ፡ ከከብቶች ጋር ሲሰራና አጋዘን ሲያድን ውሎ ሲገባ፡ ርቦት ወደ ወንድሙ መጣ። ወንድሙም፡ ትልቅ ድስት የምስር ወጥ፡ የዱር እ—አተርና ነገሮችን በአንድ ላይ፡ ፈልጎ ነበር። አንድ ሰው ቀኑን ሙሉ ከተራመደ በኋላ፡ ሲራበው በጣም አጓጊ ሊሆን ይችላል። ወንድሙም፡ "ራሴን ለመሳት ምንም አልቀረኝም። ከዚህ ስጠኝ" አለው።

እሱም፡ "እንግዲህ፡ እኔ... ብኩርናህን እንዳገኝ ከማልክልኝ" አለው። አያችሁ? እንዴት እንዳደረገው ግድ አልነበረውም፡ ዋናው ማግኘቱ ብቻ ነበር።

ብኩርናውን ሲያገኝ፡ ያ እልባት እንዳገኘ መስሎት፡ ነበር።

79 ጴንጤቆስጤ፡ የወደቃችሁት እዚያ ላይ ነው! በመንፈስ ስለተወለዳችሁ፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ስለተወለዳችሁ፡ ብኩርናን ስላገኛችሁ፥ ያ እልባት ያስገኘ መሰላችሁ ነበር። ነገር ግን ያ የሚያስጀምረው ብቻ ነው። **እርሱን ስሙት** በ—በሚለው መልእክት ውስጥ ታስታውሳላችሁ፡ ህፃኑ፡ በቤተሰብ ውስጥ ከተወለደ በኋላ፡ ወንድ ልጅ ሲሆን። የብኩርና መብት ነበረው፡ ነገር ግን መረጋገጥ ነበረበት፡ ልጁ-መስልጠን ነበረበት። ከ—ከዚያም የአባቱን ፈቃድ የሚታዘዝ ልጅ መሆኑን ካላረጋገጠ፡ ካልሆነ ግዴታ መሆን አለበት፡ እንግዲህ፡ እ—እሱ… በጭራሽ… ወራሽ አልሆነም። ምንም አልወረሰም፡ ምንም እንኳን ወንድ ልጅ ቢሆንም፡ የአባቱ ስራ የማያሳስበው ከሆነ ምንም አልወረሰም።

80 መንፈስ ቅዱስ በጴንጤቆስጤ ህዝብ ላይ በወረደ ጊዜና በቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን ስጦታዎችና ነገሮች መመለስ ሲጀምሩ፥ ከመንፈስ ስለተወለዱ፡ ያ፡ እልባት ያስገኘ መሰላቸው ነበር። እያችሁ፡ ዳሩ ግን፡ ልጅን የመሾም ሁኔታ አለ። ይህ ልጅ እውነተኛ ልጅ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ፡ ወደ ህዝብ መሃል ይወሰድና፡ ከዚያም ይቀመጥና፡ ልብሰ ቀይሮ፡ እዚያ ላይ ይቀመጣል፥ ከዚያም ልጅን መሾም አለ፡ ይህም አባቱ ያለውን ሁሉ እንደሚወርስ ነው።

81 እግዚአብሔር በልጁ በደብረ ታቦር ላይ ያደረገውም ይኸው ነው። ተጋርዶ ነበር በ… ወይም በደመና፡ ተለወጠም፡ ልብሱም እንደ ፀሐይ አበራ፡ አንድ ድምፅም፡ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" አለ። ሙሴና ህጉ ወድቀዋልና። ይሄ ደግሞ እርሱ ነው፡ "እርሱን ስሙት።" እርሱ ተሹሞ ነበር። እያችሁ?

82 አሁን ያዕቆብ ብኩርና ስላለው፡ ሁሉም ነገር የተሰራ፡ መሰሎት ነበር።

የጴንጤቆስጤ ሰዎችም እንዲሁ አድርገው ነበር፡ እነሱም መደራጀት ጀመሩ፡ ዋ—ዋንነስ፡ ትሪነስ፡ ትሪኒታሪያንስ፡ ሁሉንም ዓይነት ድርጅትና፡ እርስ በርስ መጨቃጨቅና መጎታተት ጀመሩ፡ ይህም ምልክቱ እንዳልታየ አረጋገጠ። ክፋት፡ ምቀኝነት፡ ጠብ፡ እያችሁ፡ ነገር ግን የደረሰበት ቦታ እዚያ ነበር።

83 አሁን፡ እያችሁ፡ ያዕቆብም ተመሳሳይ ነገር አሰቦ ነበር። ነገር ግን በአንድ ምሽት፡ በፍርሃት፡ ለህይወቱ፡ መጣበብ ያዘው፡ እንዲህ ብሎ ሲያስብ፡ "ከዚያ ወንዝ ማዶ፡ ወንድሜ እኔን ለመግደል እየጠበቀ ነው። ሊገድለኝ ነው" አለ። እያችሁ፡ ያገኘው ብኩርና፡ ለሞቱ ምክንያት ሊሆን የነበረው ነገር ነበር።

አንዳንድ ጊዜ የምትቀበሉት ያው ነገር፡ እንደ መንፈስ ቅዱስ፡ አዎ፡ ከመንፈስ ዳግመኛ የተወለዳችሁ፡ ካልተጠነቀቃችሁ፡ ያው ነገር በመንገዱ መጨረሻ ላይ ይፈርድባችኋል። በትክክል። ኖኅን ያዳነው ያው ውሃ፡ ዓለምን ኮነነው። እ—እክራሪነት ብላችሁ የምትጠሩት ነገር በመንገዱ መጨረሻ ላይ የሚፈርድባችሁ ያው ነገር ሊሆን ይችላል።

84 አሁን ያዕቆብ ህይወቱ ወደ መጨረሻው እንደተቃረበ አውቆ ነበር። ወንድሙ፡ በአራት መቶ የታጠቁ ሰዎች፡ እሱን ሊያገኘው እየመጣ መሆኑን የሚነግረው መልእክተኛ መጥቶ ነበር፡ በመንገዱ ላይ መሆኑን እ—አውቆ ነበር። ፍርሃት ያዘው። የሰላም መስዋዕት ከዔሳው ጋር ለማድረግ በሬዎችን፡ ከብቶችንና፡ በጎችን ይዘው ሰዎች ከፊቱ ላከ። ከዚያም፡ ከዚያ በኋላ፡ ሌላ

የሰዎች ቡድን ከሌላ ብዙ ነገር ጋር ላከ። ከዚያም ቁጣውን ለመመለስ፡ መጀመሪያ ሊገናኘው እየሞከረ፡ ሌላ ቡድን ከሌላ ብዙ ነገር ጋር መላክ ጀመረ። ከዚያም ማሰብ ጀመረ፡ “ያ እያስቆመውም፡ ምክንያቱም ምናልባት ከእኔ የበለጠ ሀብታም ሊሆን ይችላል። እያስፈልገውም።” ከዚያም ሚስቶቹንና ትንንሽ ልጆቹን ወሰደና፡ አሻግሮ ላካቸው፡ ይህም ዔሳው እነዚያን ትንንሽ ልጆችና ሚስቶቹን እንዲያይ ነው። በእርግጠኝነት በገዛ ትንንሽ የእህትና የወንድም ልጆቹ ላይ አይጨክንም፡ አይገድላቸውም። ከዚያ፡ እሱ፡ አሁንም ሊያደርገው አልቻለም። እግዚአብሔር ሰውን እንዴት እንደሚያገኝ ያውቃል። ያዕቆብ ወንዙን ተሻገረ። እዚያ ተንበርክኮ ወረደ።

ታውቃላችሁ፡ ከዚያ በፊት፡ ትንሽ አጨበርባሪ ዓይነት ነበር። አገላለጹን ይቅርታ አድርጉልኝ፡ ነገር ግን ትንሽ... ያዕቆብ ነበር። **ያዕቆብ** ማለት “አታላይ” ማለት ነው፡ እሱም እንደዚያ ነበር። ነገር ግን በእሱ ላይ መፈጸም ያለበት ነገር ነበረ። እዚያ መጣበብ ውስጥ፡ እዚያ ሞት በፊቱ ሲደቀን...

85 ዛሬ ማታ እዚህ የተቀመጡ ወንዶችና ሴቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡ እነሱም፡ ሞት ልክ በፊታችሁ ተደቅኗል። እናንተም የምትፈልጉትን ነገር ማግኘት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ፡ በመጣበብ መምጣት ነው። “ዛሬ ማታ፡ ማግኘት አለብኝ። አሁን አገኘዋለሁ፡ አለበለዚያ አብቅቶልኛል። ነገ በጣም ዘግይቷል። አሁን ማግኘት አለብኝ!”

ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ለምልክቱ ሰትጸልዩ፡ “እንግዲህ፡ አሁን ሄጄ እሞክራለሁ። ጌታ ሆይ፡ እኔ፡ ትንሽ ደክሞኛል፡” አትበሉ። ኦህ፡ ምህረት፡ ወንበራችሁ ላይ ቆዩ! ምንም ዓይነት ሙ—ሙከራ አታድርጉ። መጥታችሁ፡ “በጸሎት መሰመር ውስጥ እልፋለሁ፥ በራሴ ላይ ዘይት ይቀቡኛል፡ የሚጠቅመኝ ከሆነም እያለሁ፡” የምትሉ ከሆነ፡ ባላችሁበት ብትቀመጡ ይሻላል። ወደዚያ ቦታ እስክትደርሱ ድረስ፡ መላው ቤተክርስቲያን፡ በሞትና በሕይወት መካከል ወዳለበት ቦታ እስኪደርስ ድረስ፡ አሁን ልታገኙት ይገባል አለበለዚያ ትጠፋላችሁ፡ ከዚያም እግዚአብሔር ወደ ሰፍራው ይመጣል። እግዚአብሔርን ወደ ሁኔታው ለማምጣት መጣበብን ይጠይቃል።

86 ያዕቆብ ከዚህ በፊት አልቅሶ በማያውቀው ሁኔታ አለቀሰ። አምላክን እስኪያገኝ ድረስ በመጣበብ ጮኸ። ሲያገኘውም፡ ታገለ፥ ለአስራ አምስት ደቂቃ ብቻ አልነበረም። ሌሊቱን ሙሉ በነፍሱ ውስጥ፡ አብሮት እንዲቆይ፡ ታገለ፥ አሁንም በረከቱን እንዳላገኘ ያውቅ ነበር፡ በረከቱ እስኪመጣም ድረስ አጥብቆ መያዝ ቻለ። በረከቱ እስኪመጣ ድረስ በመጣበብ ታገለ። ከዚያም፡ ሲያይም... እግዚአብሔር በሰፍራው እስኪገኝ ድረስ። ከዚያም፡ በመጠባብ፡ በረከቱ በእርሱ ላይ ሲወርድ መሰማት ሲጀምር፡ “አልለቅህም” አለው።

ብዙ ሰዎች፡ “ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡ አሁን አግኝቼዋለሁ” ይላሉ። እዚያ ላይ ተታላችኋል። አዎ! አንድ ሰው፡ “ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ በጣም ደስ የሚል ስሜት ተሰምቶኛል፡ ወደዚያ ወርጄ ጸለይኩ። ኦህ፡ መንቀጥቀጥ በላዬ ላይ መጣ” ይላል። ያም እግዚአብሔር ሊሆን ይችል ይሆናል። “በፊቴ ታላቅ ብርሃን አየሁ።” ያም አሁንም እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን እያወራሁ ያለሁት ስለዚያ አይደለም።

87 መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው፡ በዕብራውያን 6ኛው ምዕራፍ ላይ፡ “ዝናብ በጻድቃንም በኃጢአተኞችም ላይ፡ በእኩል ይዘንባል” ይላል። አሁን፡ ስንዴ ወሰዳችሁ፡ እንክርዳድንም ወሰዳችሁ፡ በማሳው ላይ ብትዘሩት። ዝናቡም በእርግጥ የተላከው ለስንዴው ነው፡ ዳሩ ግን ዝናቡ በስንዴው ላይ እንደሚዘንበው ሁሉ በእንክርዳዱም ላይ ይዘንባል። በተጨማሪም፡ በዝናቡ፡ እንክርዳዱም ስንዴው በዝናቡ ደስ እንደሚለው ሁሉ እጅግ ይደሰታል፡ የሚዘንበውም ያው አንድ ዓይነት ዝናብ ነው። ያው መንፈስ ቅዱስ በማያምን ሰው ላይ ሊወርድበት አማኝ በሚያደርገው ልክ በተመሳሳይ መንገድ እንዲያደርግ ሊያደርገው ይችላል። ነገር ግን በፍሬያቸው ይታወቃሉ፥ እያወራሁ ያለሁትም ስለዚያ ነው፡ ምልክቱ ያ ነው። ዱ-...

88 ይልቁንም፡ ያዕቆብ፡ በመጣበብ፡ እንዲህ አለ፡ “እንደተሰማኸኝ አውቃለሁ፡ አብረኸኝ እዚህ ነህ፡ ነገር ግን አልለቅህም” አለ።

አንዳንድ ሰው፡ በመጀመሪያዋ አነስተኛ ስሜት ጥሩ መስሎ ይታየዋል፡ ተነስቶም ወደ-ላይ ወደ-ታች ይዘላል፡ በመተላለፊያውም ላይ እየሮጠ፡ “አግኝቼዋለሁ፡ አግኝቼዋለሁ፡ አግኝቼዋለሁ፡” ይላል። ኦህ፡ አይደለም። ኧ-ህ። አይደለም።

ያዕቆብ የተለየ አረማመድ እንዲራመድ እስኪያደርገው፡ የተለየ ሰው እስኪያደርገው ድረስ፡ የሆነ ነገር እስኪፈጠር ድረስ እዚያው ቆየ፡ ምክንያቱም ያ እስኪሆን ድረስ እዚያው ስለቆየ ነው። ቻለ... መጽሐፍ ቅዱስ፡ “እስኪያሸንፍ ድረስ ያዘው” ይላል። ሰው እንዴት እግዚአብሔርን ሊያሸንፍ ይችላል? ነገር ግን ልታደርጉት ትችላላችሁ። ልታደርጉት ትችላላችሁ። ሰው እግዚአብሔርን ሊያሸንፍ ይችላል።

89 አንድ ጊዜ ሕዝቅያስ የሚባል ሰው ነበር፡ ነቢዩም፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ትሞታለህ” ብሎ ነገረው። ሕዝቅያስ ፊቱን ወደ ግድግዳው አዞረ፡ በመጣበብም ሆኖ አለቀሰ፡ “ጌታ ሆይ፡ እሰበኝ። በፊትህ በፍጹም ልብ ተመላልሻለሁ፡ አስራ አምስት ተጨማሪ ዓመታትም ያስፈልገኛል፡” እግዚአብሔርም የሆነ ነገር እንደሚሆን፡ እንደሚሞት ከነገረው በኋላ እንዲህ በማለት አለቀሰ። እናም፡ በመጣበብ፡ የእግዚአብሔርን እቅድ ቀየረ። መጣበብ፡ ሆኖም፡ በመጣበብ እጅግ አምርሮ አለቀሰ።

90 ያዕቆብ በረከቱ እስኪመጣ ድረስ እዚያው ቆየ፡ ስሙም “አታላይ” ከሚለው ወደ “ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ልዑል” ተቀየረ። ሕዝብ እንኳ በሰሙ ተጠራ። አዎ፡ ጌታዬ! ምን ነበር? ውጤቱ ስለጉዳዩ በመጣበቡ ምክንያት ነበር። በሚቀጥለውም ቀን ዔሳውን ሲያገኘው፡ ምንም ዓይነት ጠባቂዎች አላስፈለጉትም። በቀጥታ ወጥቶ አገኘው። አያችሁ? ለምን? ማረጋገጫውን እስኪያገኝ ድረስ በመጣበብ ውስጥ ገብቶ ነበር።

ማረጋገጫውን እስክታገኙ ድረስም ትጣበባላችሁ። ይህን ካላደረጋችሁ፡ እንዲጸልይላችሁ እንኳ አትምጡ። ወደ መሠዊያው ለመሄድ እንኳ አትምጡ። በሕይወትና በሞት መካከል እስኪሆን ድረስ ጠብቁ፡ ከዚያም የሆነ ነገር ይፈጠራል። በእርግጠኝነት፡ መጣበብ!

91 ሩት አንድ ጊዜ፡ በኑኃሚን እጠገብ ቆማ ሳለች፡ ተጣበበች። ወደ ወገኖቿ፡ ወደምትወዳቸው ሁሉ፡ ወ—ወደ አመለከቻቸው፡ አማልክቶቿና

ህዝቧ መመለስ ይኖርባታልን፡ ወይስ ከኑኃሚን ጋር ትጣበቃለች? ምን ማድረግ አለባት? በመጣበብም ውስጥ ገብታ፡ እንዲህ ብላ አለቀሰች፡ “ወደምትሄጂበት፡ እሄዳለሁ። በምትኖሪበት፡ እኖራለሁ። በምትሞቺበት፡ እሞታለሁ። በምትቀበሪበት፡ እቀብራለሁ... ማለቴ እቀበራለሁ። አምላክሽም አምላኬ ይሆናል” ብላ ጮኸች። ይኸውና አያችሁ፡ ተጣበበች! እግዚአብሔር ባረካት፡ ወንድ ልጅ፡ ኢዮቤድን ሰጣት። ኢዮቤድ እሴይን ወለደ። እሴይም ወለደ፡ በእሴይም በኩል፡ ኢየሱስ መጣ። ምክንያቱም፡ መጣበብ!

92 እንደ ትንሿ ጋለሞታ፡ ረዓብ፡ እሷም ተጣብባ ነበር። ሞት በፊቷ እንደተጋረጠ አውቃ ነበር። ከፍርድ በታች ነበረች። በመጣበብም ውስጥ ገብታ፡ እንዲህ አለች፡ “እናንተን ሰላዮችን እደብቃለሁ። ማንኛውንም ነገር አደርጋለሁ። ብቻ፡ በአምላካችሁ ማሉልኝ፡ ቤቴም ጸንቶ ይቆማል” አለች። ይኼውና አያችሁ።

እርሱም፡ “እኔ... ይህን ምልክት ከወሰድሽ፡ ይሆናል” አላት።

93 ኤሊዔዘር ለይስሐቅ ሙሽራን የመፈለግ ኃላፊነት በተጣለበት ጊዜ ተጣብቦ ነበር። የደማስቆው ኤሊዔዘር ታላቅ ሰው ነበር። በአብርሃም ዘንድ ሞገስን አግኝቶ ነበር፡ ለልጁ ለይስሐቅም ትክክለኛዋን ዓይነት ሙሽራ፡ ወጥቶ እንዲፈልግ፡ በአብርሃም፡ ታምኖ ነበር። በዚያም በኩል ክርስቶስ ይመጣ ነበር።

94 አሁን፡ ኤሊዔዘር፡ መንፈሳዊ ሰው በመሆኑ፡ ምን ማለት እንደሆነ አውቆ ነበር። ትክክለኛዋ ዓይነት ሴት የ—የዚያ ሰው ሚስት መሆን ነበረባት። ታዲያ እንዴት ይመርጣታል? በመጣበብ ጊዜው፡ ወደ ከተማይቱ በደረሰ ጊዜ፡ ጸለየና፡ “ጌታ አምላክ ሆይ” አለ! ይሄው ነው በቃ። ሰትጣበቡ፡ ወደ መጸለይ ሂዱ። “ጌታ አምላክ ሆይ፡ ወጥታ ግመሎቹን የምታጠጣና፡ እኔንም የምታጠጣኝ የመጀመሪያዋ ልጃገረድ፡ እርሷ ትሁን።” በመጣበብ ውስጥ በገባበት ሰዓት ጸለየ።

95 ቆንጆዋ ልጃገረድ፡ ርብቃ፡ መጣች፡ ግመሎቹንም አጠጣች። ከዚያም፡ “በመንገዴ ላይ አታዘግዩኝ” አለ። ትሄድ እንደሆነ የምትወስንበት የውሳኔ ጊዜ ላይ መድረስ ነበረባት። እሷ የሙሽራይቱ ምሳሌ ነበረች። እ—እሷ ፈጽሞ አይታው የማታውቀውን ሰው ሄዳ ታገባለችን? አሁን፡ ያ ታላቅ ነገር ነው። ፈጽሞ እንኳ ሳታየው፡ ዳሩ ግን በአገልጋዩ በኩል ብቻ ሰምታ ነበር።

96 ያ የሙሽራይቱ ምሳሌ ነው። እናንተም ክርስቶስን ፈጽሞ አላያችሁትም። ዳሩ ግን፡ እርሱ ምን እንደሆነ፡ በአገልጋዮቹ በኩል ትሰማላችሁ። እርሱን ለማግኘት ለመሄድ፡ ሁሉንም ነገር ትሸጣላችሁ፡ ቤቶቻችሁን፡ ሌላውንም የሚጠይቀውን ሁሉ ትተዋላችሁ። አሁን አስተውሉ፡ የሙሽራይቱ ምሳሌ፡ የሐይማኖት ተቋም ቤቷን ትታ፡ አያችሁ፡ ለመሄድ፡ ውሳኔዋንም አደረገች።

97 ዮናስ፡ በማዕበል ጊዜ ከመርከብ ወደ ውጭ ተወረወረ፡ በባሕሩ ግርጌ፡ በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ገባ። በሕይወት የመትረፍ ተስፋ ሁሉ ጠፍቶ ነበር። ዳሩ ግን ሰሎሞን፡ ቤተ መቅደሱን ሲቀድስ፡ “ጌታ ሆይ፡ ሕዝቡ በየትኛውም ስፍራ ችግር ውስጥ ቢሆኑ፡ ወደዚህ ቤተ መቅደስ ፊታቸውን አዙረው ቢጸልዩ፡ ከዚያም ሰማ” ማለቱ፡ ወደ አእምሮው መጣ። በአሳ ነባሪው ሆድ ውስጥም እየተንከባለለ፡ እንዴትም በጉልበቱ እንደተንበረከከ፡ አስባለሁ፡ የአሳ ነባሪው ትውከት በላዩ ላይ ሁሉ እንደሞላበት ተንበረከከ።

በዚያም በመጣበብ ጸለየ። በዚያም ውስጥ፡ ተጠበበ፥ በእሳ ነባሪው ሆድ ውስጥ የነበረው ጥቂት የኦክስጅን እስትንፋስ ብቻ ነበር። በነዚያም በሚሰባቸው ጥቂት እስትንፋሶች፡ ምናልባትም በየትኛው አቅጣጫ እንዳለ አያውቅም ነበር፡ እንዲህም አለ፡ “ጌታ ሆይ፡ ወደ ቤተ መቅደስህ ወደ ላይ እየተመለከትኩ እንደሆነ አምናለሁ።” ሊያልቅ ጥቂት እስትንፋሶች ብቻ ሲቀሩት፡ በመጣበብ፡ በእነዚያ ሁኔታዎች ስር፡ ጸለየ። ከዚህ በፊት ፈጽሞ ተደርጎ አያውቅም፡ ዳሩ ግን እርሱ ተጣብቦ ነበር። ጸለየ፡ እግዚአብሔርም ለሦስት ቀናትና ሌሊቶች በሕይወት አቆየው፡ መልእክቱንም እንዲያደርስ በተገቢው ስፍራ አወጣው። መጣበብ!

98 ሐና፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካን የነበረች ሴት፡ ወንድ ልጅ ፈለገች፡ ስለ እርሱም መጸም ጀመረች። በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረው ካህን እንኳ ሰክራለች ብሎ እስኪገምታት ድረስ ጾመች ጸለየችም። እጅግ በመጣበብ ውስጥ ነበረች! የተቀሩት ሴቶች ሌላዋ ምን ዓይነት ቆብ እንዳደረገች ይመለከቱ ነበር፥ እንዴት እንደሚሆን ታውቃላችሁ፥ ሌላዋም ምን ዓይነት ልብስ እንደለበሱ ትመለከት ነበር፡ በእርሻውም ላይ ስለሚከናወኑ ነገሮች ያወሩ ነበር። ዳሩ ግን ሐና አይደለችም፥ እርሷ በቀጥታ በሕዝቡ ሁሉ መካከል አልፋ ወደ መሠዊያው ሄደች። እየጾመችም ነበር። ነቀፋዋ እንዲወገድላት ፈለገች።

ዛሬ ምንኛ የተለየ ነው። ልጅ መውለድ ልክ እንደ ነቀፋ ሆኗል። በ—በዚያን ጊዜ ግን አለመውለድ ነቀፋ ነበር።

በጉልበቷም ተንበረከከች። የቤተ መቅደሱንም ክብር ፈጽሞ አላስተዋለችም። የተከበረ ካህን ሲወጣ ፈጽሞ አላስተዋለችም። እንባዋ በጉንጮቿ ላይ እስኪፈስ ድረስ እጅግ በጭንቀት ውስጥ ነበረች፡ በመጣበብም፡ እያለቀሰች ነበር፡ “ጌታ አምላክ ሆይ፡ ወንድ ልጅ ስጠኝ። ወንድ ልጅ ስጠኝ!”

99 እስተውሉም፡ እሷ፡ ራስ ወዳድ አልነበረችም። እግዚአብሔር ሲሰማት፡ ጸሎቷንም መልሶ ወንድ ልጅ ሲሰጣት፡ ለእግዚአብሔር መለሰችው። እግዚአብሔር ጸሎቷን ከመለሰላት በኋላ ራስ ወዳድ ላለመሆን ፈቃደኛ ስለነበረች፡ ነቢይን ሰጣት። ኦህ፡ ያ ተጨማሪ በረከት ነበር። ኦህ፡ እርሱ በሚሰጣቸው እነዚያ ጥቃቅን ተጨማሪ ነገሮች፡ እጅግ የተሞላ ነው። ወንድ ልጅ ብቻ ሳይሆን፡ ነቢይንም ጭምር። በእስራኤልም ውስጥ፡ ለብዙ ዓመታት፡ ምንም ዓይነት ግልጽ ራእይ አልነበረም። ሳሙኤል፡ የመጀመሪያው ነቢይ፡ ለብዙ፡ ለብዙ ዓመታት፡ አንዲት እናት ስለተጣበበች፥ ልጆች መውለድ ስላልቻለች፡ የመውለጃ ዕድሜዋንም ስላለፈች፡ ምናልባትም ሰልሳ፡ ሰባ ዓመቷ ነበር። በመጣበብም ጸለየች፡ ይህን ልጅ ማግኘት አለባት! ምን ነበር? እግዚአብሔር ለልቧ ተናግሮት ነበር፡ ምንም ጥርጥር የለውም።

100 እግዚአብሔር እስኪናገራችሁ ድረስ ልትጣበቡ አትችሉም። ኦህ፡ ቤተክርስቲያን ሆይ፡ በዚህ ሰዓት ተነሽ እራስሽንም እራግፊ! ሕሊናችሁን ቀሰቅሱት፡ በዚህ ዘመን፡ እራሳችሁንም አንቁ! መጣበብ አለብን፡ አለበለዚያ እንጠፋለን! ከጌታ ዘንድ የሆነ ነገር እየመጣ ነው! ይህንንም እንደ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** አውቀዋለሁ። የሆነ ነገር እየመጣ ነው፡

ብንጣበብ ይሻለናል። በህይወት እና በሞት መካከል ነው። በእኛም ውስጥ ያልፋል እኛም አናየውም።

101 ምክንያቱም ራስ ወዳድ ስላልነበረች፡ ነቢይ ተሰጣት።

102 ሱነማዊቷ ሴት እሷ ያረጀች ብትሆን ባሏም ያረጀ ቢሆንም፡ ነቢዩ የጌታን ቃል የተናገረለት ትንሽ ልጅ ተሰጣት። ልጆች አልነበሯቸውም፡ ዳሩ ግን ለ—ለዚህ ነቢይ ደግ ነበረች። እሱም የእግዚአብሔር ሰው እንደሆነ አውቃ ነበር። የተከበረ፡ እውነተኛ ሰው መሆኑን አስተዋለች። ወደ ቤት መጣ፡ ባሏ በዚያ አልነበረም፡ ሌላም ምንም ነገር አልነበረም። እሱ ቅዱስ ሰው ነበር። እርሱ የተከበረ ሰው መሆኑን ሊያዩ ችለዋል። ምልክቶችንና ድንቆችን ሲያደርግ አይታ ነበር። የሆነውን ነገር ሲናገር ሰምታዋለች። እርሱ የተከበረና፡ ቅዱስ ሰው ነበር።

እሷም፡ “ይህ ወደ እኛ የሚመጣው ሰው ቅዱስ ሰው እንደሆነ አስተውያለሁ” ብላ ለባሏ ነገረችው። የቤቱ እመቤት፡ እሱ ቅዱስ ሰው መሆኑን አውቃ ነበር። እርሱም እንዳያፍር ብላ፡ በዚያ ትንሽ ቤት ሠራችለት። በፈለገበት ጊዜም መምጣት ይችል ነበር፡ ወዘተ። እ—እዚያም ትንሽ አልጋ፡ ራ—ራሱን መታጠብና፡ የሚጠጣውንም ማግኘት እንዲችል፡ የውሃ ማሰሮና ወዘተ አስቀመጠችለት። በመቀጠልም ምናልባትም አገልጋይዋን፡ ወይም የሆነ ሰውን፡ ምግብ የሚያዘጋጀውን ሰው፡ እንዲያበላው ከ—ከምግብ ጋር ልካ ይሆናል፡ መጥታም የ—የዕለቱን ሰላምታ ትሰጠው ይሆናል፡ ወይም ሌላ ነገር።

103 ስለዚህም፡ ኤልያስ፡ ይህ የተደረገለትን ደግነት ባየ ጊዜ... እንዲህ ተብሎም ተጽፏል፡ “ለእነዚህ ለታናናሾቼ ያደረጋችሁትን፡ ለእኔ አደረጋችሁት።” ስለዚህ ያንን አየች፡ ሴትዮዋም እግዚአብሔርን በነቢዩ ውስጥ እንዳየችው ሁሉ፡ ነቢዩንም በማክበር እግዚአብሔርን እያከበረች ነበር። ስለዚህም፡ ለዚያ፡ ምንም ነገር አልፈለገችም። ምንም ነገር በልቧ ውስጥ አልነበረም። ያደረገችው እግዚአብሔርን ስለምትወድ ብቻ ነው። ለማንኛውም በረከት ብላ አላደረገችውም። ዝም ብላ አደረገችው።

104 አሁን፡ አሁን ኤልያስ እንዲህ አለ፡ “ሂድና ጠይቃት፡ ስለ እርሷ ለንጉሥ ልናገርላትን? የግል ጓደኛው ነኝ። ወይም፡ ለሠራዊት አዛዡ ልንገረው፡ እ—እርሱን በደምብ አውቀዋለሁ። የሆነ ውለታ፡ ላደርግላት የምችለው የሆነ ነገር አለ፡ ለእኔ ለሆነችበት ነገር የሆነ ነገር ልሰጣት እፈልጋለሁ። መ—መግባኛለች። በአልጋዎቹም ላይ እንዳንቀላፋ አድርጋኛለች። ለ—ለእኛ በጣም ጥሩ ነበረች። አሁን ምን ላድርግላት? ”

እሷም፡ “አይ፡ እኔ በሕዝቤ መካከል ብቻ እኖራለሁ። እ—እኛ ደህና ነን። ኑሮ አለን፡ ያ ነው በቃ። ምንም ነገር አያስፈልገንም” አለች።

ግያዝም፡ “ነገር ግን ምንም ልጆች የሏትም” አለው።

105 ግያዝ ያንን እንዳየ ወዲያው፡ ነቢዩ ራእይ እንዳየ ምንም ጥርጥር የለውም፡ ምክንያቱም እርሱ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**። ሂድና ንገራት፡ በተገቢው ጊዜ፡ ወይም በትክክለኛው ጊዜ፡ ከአንድ ዓመት በኋላ፡ ወንድ ልጅ ታቅፋለች” ብሏልና።

106 ልጁም ተወለደ። የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ እያለ… እነዚያ አረጋውያን ባልና ሚስት ይህን ትንሽ ልጅ፡ ብቸኛ ልጃቸውን እንዴት ይወዱት እንደነበር አስቡ። አንድ ቀንም ከአባቱ ጋር፡ ስንዴ ሊያጭድ ወጥቶ ነበር። የቀኑ እኩሌታ ገደማ ነበርና፡ የፀሐይ ምች መታው፡ ብዬ እገምታለሁ፡ ምክንያቱም፡ "ራሴን" እያለ መጮህ ጀምሮ ነበር። እያመመውም እያመመውም ሄደ። አባቱም ከእርሻው ሊያወጣው ግድ ሆነበት፡ በዚያም እንዲህ ያለ የድንገተኛ አደጋ ስለነበር፡ አገልጋይ ላከ፡ ወደ ውስጥም ላከው።

107 እናትየው እስከ ቀትር ድረስ በጭኗ ላይ አድርጋ ያዘችው፡ እርሱም ሞተ። ልብ በሉ፡ በነቢይ ጸሎትና ተሰፋ፡ የተሰጣት ብቸኛው ልጇ፡ እንዲሁም **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** በሚለው ቃል አማካይነት በጌታ የተሰጣት። አንድ ቦታ ላይ የተሳሳተ ነገር እንዳለ ታውቅ ነበር። እንዲህ ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር እንዴት ያንን ልጅ ሰጥቶ ፍ—ፍቅሯ በዚያ ሕፃን ላይ እንዲያርፍ ያደርጋል? ሰጠኝ ብላ ያልለመነችው ልጅ ሆኖ ሳለ። ለመውለድ ዕድሜዋ ገፍቶ ነበር። የእግዚአብሔር እጅ ሊያውጀው ግድ ነበር። እነሆ ይህ ሰው ተናገረ፡ ነብዩ። በዚያም ይህ ሕፃን በዚህ ሁኔታ ውስጥ፡ ሞቶ ነበር፡ ብቸኛ ልጇ።

ስለዚህ ለአገልጋዩ፡ "በቅሎ አዘጋጅልኝ፡ አንተም ጋልብ፡ ፈጽሞም እንዳታቆም። ማንም ሰው ሊያቆምህ ቢሞክር፡ አንዲት ቃል እንኳ አትናገር፡ በቀጥታም ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ንዳ። እዚያ ላይ በአንድ ዋሻ ውስጥ፡ ወደ ኋላ ገለል ብሎ፡ የልዑል እግዚአብሔር አገልጋይ አለ፥ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ሕፃን ልጅ ትወልጃለሽ ብሎ የነገረኝ፡ እሱ ነው። እግዚአብሔር ይህን ለምን እንዳደረገ ማወቅ እፈልጋለሁ" አለች። ስለዚህ እርሱም አለ… "ቀጥታ ወደ ፊት ሂድ በቅሎውንም አትግታው። ባለው ኃይሉ ሁሉ ይሩጥ። እዚያ እስክትደርስ ድረስ ይሩጥ።" መጣበብ!

108 ነቢዩ ኤልያስም ተነስቶ፡ ተመለከተ፡ እንዲህም አለ፡ "ያቺ ሱነማዊት መጣች፡ እነሆ፡ እሷ፡ የሆነ ችግር ገጥሟታል። እግዚአብሔር ከእኔ ሰውሮታል። ችግሩ ምን እንደሆነ አላወቅሁም።" እንዲህ አለ፡ "ሂድ፡ አግኛት። እ… እንፍጠን። የሆነ ችግር አለ።"

መጣበብ በነቢዩ ላይ ወረደ፡ መጣበብ በሴትዮዋ ላይ ወረደ። አያችሁ፡ አብረው እየተገናኙ ነበር፥ አንዷ የጌታ ቃል ምን እንደሆነ ማወቅ ስትፈልግ፡ ሌላው ደግሞ የጌታ ቃል ምን እንደሆነ አያውቅም ነበር። ይኸውና። አንዷ ማወቅ ስትፈልግ፡ ሌላኛው ደግሞ አያውቅም። ሴትዮዋ ማወቅ ፈልጋለች፡ ነቢዩ ግን አያውቅም ነበር። "እግዚአብሔር ከእኔ ሰውሮታል። ስትመጣ ምን እንደምላት አላውቅም፡" አለ።

በዚያን ጊዜም ልትደርስ ተቃርባ ነበር። እጁንም አንስቶ፡ እንዲህ አላት፡ "ደህና ነሽን? ባልሽስ ደህና ነውን? ልጁስ ደህና ነውን? "

109 አሁን፡ ሴትዮዋ የመጣበቧ የመጨረሻ ጫፍ ላይ ደርሳለች። እርሷም፡ "ሁሉ ሰላም ነው" አለች! ክብር ይሁን! "ሁሉ ሰላም ነው!" መጣበቧ አብቅቶ ነበር። የጌታን አገልጋይ አግኝታዋለች። እርሱ እዚያ ባይኖር ኖሮ፡ አሁንም በመጣበብ ውስጥ ትሆን ነበር። ነገር ግን፡ አያችሁ፡ እርሱ እዚያ ነበር። እርሷም፡ "ሁሉ ሰላም ነው" አለች!

ኤልሳዕም፡ “ታዲያ፡ አሁን ምን ተፈጠረ” ብሎ አሰበ?

110 ስለዚህም ሮጣ ሄዳ ከእግሩ ስር ወደቀች። ያም በመጠኑ ያልተለመደ ይመስል ስለነበር፡ ግያዝ ሊያነሳት ሞከረ። “ተዋት፡ ያንን አታድርግ፡” አለው። ኤልያስ አገልጋዩን፡ “ያንን አታድርግ። ተዋት። የሆነ ችግር ነገር አለ። እግዚአብሔር ከእኔ ሰውሮታል” አለው። ከዚያም ሕፃኑ መሞቱን ገለጠችለት።

111 አሁን፡ ነቢዩ ምን ማድረግ እንዳለበት አላወቀም ነበር። እንዲህም አለ፡ “ግያዝ፡ የምመረኮዝባትን ይህችን በትር ውሰድ።” የነካው ሁሉ የተባረከ እንደሆነ ያውቅ ነበር፡ ምክንያቱም እርሱ ሳይሆን፡ በእርሱ ውስጥ ያለው እግዚአብሔር ስለነበር ነው። ማን እንደሆነ ያውቅ ነበር። እርሱ ነቢይ እንደሆነ ያውቅ ነበር። ስለዚህም ይህችን በትር አንስቶ እንዲህ አለ፡ “ግያዝ፡ ይህችን ውሰድ፡ ሄደህም በሕፃኑ ላይ አኑረው። ማንም ሰው ቢያናግርህ፡ በመጣበብ ውስጥ ሁን። ለማንም ሰላምታ አትስጥ፡ ማንም ደግሞ... መሄድህን ቀጥል፡ ለማንም ሰው አትናገር። በሕፃኑ ላይ አኑረው” አለው።

112 ሆኖም፡ ለሴትዮዋ፡ ያ መጣበቧን አላቆመውም። የመጣችበትንም ዓላማ አላረካውም። እርሷም፡ “ሕያው እግዚአብሔርን፡ ሄደህ ለሕፃኑ እስክታገለግል ድረስ አ—አልለይህም” አለች።

113 ኤልያስም ተጠበበ። እርሱም ከሴትዮዋ ጋር፡ በመንገድ፡ ወረደ። እዚያም ሲደርሱ፡ የ... ሕዝቡ ሁሉ በግቢው ውስጥ ሆነው፡ ይጮኹና ያለቅሱ ነበር። ሴትዮዋም ሊደረግ የሚችለውን ከሁሉ የተሻለና ተገቢ ነገር አድርጋ ነበር። ሕፃኑን ወስዳ ኤልያስ ይተኛበት በነበረው አልጋ ላይ አጋድመዋው ነበር። ያም እንደ በትሩ እኩል ጥሩ ነበር። በዚያም አልነቃም ነበር፡ ስለዚህም ነገሩ ሊሰራ አልቻለም። የተለየ ነገር ማወቅ ትፈልግ ነበር።

114 ነቢዩም ገባ። አሁን በመጣበብ ውስጥ ነው። አሁን ምን ሊያደርግ ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም በመጣበብ ሆኖ፡ ወለሉ ላይ ወዲያና ወዲህ ይመላለስ እንደነበር እናገኛለን። “ጌታ ሆይ፡ ሌላ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። ይኸው መጥቻለሁ። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ብዬ፡ ለዚያች ሴት ያንን እንድናገር ነግረኸኛል። ልክ እንደነገርኳትም ሆኖ ነበር፡ ምክንያቱም አንተ ነግረኸኝ ነበርና። አሁን፡ እርሷ በችግር ውስጥ ነች፡ እኔም ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። የሞተ ልጅ እዚያ ተጋድሟል። ጌታ ሆይ፡ ምን ማድረግ እችላለሁ? ”

115 ያለምንም ጥርጥር መንፈስ ቅዱስ፡ “እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ ከሆነ፡ በሕፃኑ ላይ ተጋደም” አለው። በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ ቆመ፡ ሮጠም እጁን በእጁ ላይ፡ አፍንጫውን በአፍንጫው ላይ፡ ከንፈሩንም በከንፈሩ ላይ አኖረ። በላዩ ላይ በተጋደመ ጊዜም፡ ሕፃኑ ሰባት ጊዜ አስነጠሰ። መጣበብም አበቃ።

ሕፃኑ ሕያው ሆነ፡ ምክንያቱም ያ መጣበብ ሴትዮዋን ወደ ነቢዩ እንድትሄድ ገፍቷታልና፡ መጣበብም ነቢዩን ወደ ሕፃኑ እንዲሄድ አድርጎታልና። በሁለቱም ውስጥ የነበረው መጣበብ እግዚአብሔርን ወደ ስፍራው አመጣው። በእግዚአብሔር ፍቅር፡ ለሕዝቡም ባለው ፍቅር፡ የእግዚአብሔርን ፍቅር ወደ ታች አውርዶታል፡ እምነትንም ወደ ጦር ግንባር አውጥቶታል፡ ሥራውም

ተከናውኖ ነበር። ጉዳዩ ተዘግቷል። አሜን! ይኼው ነው በቃ። መጣበብ ይህንን ያደርጋል። በእርግጠኛነት! ጥላው አትሄድም ነበር።

116 ዕውሩ በርጤሜዎስ እዚያ በር ላይ ተቀምጦ፡ ምጽዋት፡ የሚለምን ዕውር፡ ኢየሱስ ጥሎት የሚያልፍ መስሎት ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ ድምጽ ሰማ፥ ኢየሱስ እያለፈ ነበር። እርሱም፡ "የሚያልፈው ማነው" አለ? አንድ ሰው ገፋ አድርጎ ጣለው። እርሱም፡ "እባካችሁ፡ አንድ ሰው፡ የሚያልፈው ማነው" አለ?

ከመካከላቸው አንዷ፡ እንግዲህ፡ ምናልባት አንዲት ደግ ምስኪን ደቀ መዝሙር ሴት፡ እንዲህ አለችው፡ እንዲህ አለች፡ "ጌታዬ፡ ያ የሚያልፈው ማን እንደሆነ አታውቅም እንዴ? "

"አላውቅም። አንዳንዶቹ እንዲህ ሲሉ እሰማለሁ፡ 'እዚህ ላይ የሞቱ ሰዎች የሞሉበት ሙሉ የመቃብር ሰፍራ አለ። ሙታንን የምታስነሳ ከሆነ፡ ሂድና አስነሳቸው' ይላሉ። ተሳዳቢው ነው ወይስ ማነው? "

"አይደለም። ስለዚያ የገሊላ ነቢይ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ ስለሚባለው ወጣት ነቢይ ሰምተህ ታውቃለህ? "

"አላውቅም።"

"እንግዲህ፡ ታውቃለህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጥቅልል መጻሕፍቶቻችን ላይ የዳዊት ልጅ በዙፋኑ ላይ ሊቀመጥ እንደሚነሳ ይናገራል። ያ እርሱ ነው።"

"ያ እርሱ ነውን? ያ እርሱ ነውን፡ እያለፈ ነውን? "

መጣበብ እንዲህ ብሎ እንዲጮኽ ገፋፋው፡ "ኦ ኢየሱስ፡ አንተ የዳዊት ልጅ ሆይ፡ ማረኝ!"

> እዳኝ ሆይ፡ አትለፍብኝ፡
> ጸሎቴን ሰማ፥
> ህዝብህ ጸጋህን ሲያገኝ፡
> አትለፍብኝ።

"ኦ፡ ኢየሱስ!"

አንዳንዶቹም፥ "ዝም በል! በጣም ትረብሻለህ" አሉት።

117 ሆኖም እርሱ በመጣበብ ውስጥ ነበር። ጥሎት ካለፈ፡ ሌላ ዕድል በድጋሚ ላያገኝ ይችላል። እኛም ላናገኝ እንችላለን፥ ይህ የመጨረሻው ምሽት ሊሆን ይችላል። መጣበብ! እርሱም "ኦ፡ ኢየሱስ፡" ብሎ ጮኸ! ማንም ሰው እንዲያቆም ቢነግረውም፡ እርሱ በተመሳሳይ ሁነታ ጮኸ፡ እንዲያውም በበለጠ ድምጽ። ዝም እንዲል ሲነግሩት፡ ይበልጥ እንዲጮኽ አደረገው። በመጣበብ ውስጥ ነበር። ማንም ሊያቆመው አልቻለም። "አንተ የዳዊት ልጅ ሆይ፡ ማረኝ!" እርሱም በመጣበብ ጮኸ።

118 የእግዚአብሔርም ልጅ፡ የዓለምን ኃጢአት በጫንቃው ላይ ተሸክሞ፡ ልክ በዚያን ጊዜ፡ ስለ ዓለም መሰዋዕት ሆኖ ለመቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ ሳለ፡ በመንገዱ ላይ ቆመ። መጣበብ፡ የተሰፋ መቁረጥ ጩኸት፡ የእግዚአብሔርን ልጅ አቆመው። አለውም፡ "ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ? " ኦህ!

እርሱም፡ “ጌታ ሆይ፡ አይ ዘንድ” አለ።

እርሱም፡ “በመንገድህ ሂድ፡ እምነትህ አድኖሃል” አለው።

ያ በቂ ነበር። መጣበብ! መጣበብ አንድን ነገር ለመቀበል ሲሆን፡ በጣም ደካማዋን ትንሽ ንክኪ እንኳ፡ እምነት ያቺን ይይዛታል። አያችሁ? እንዲህ አላለም፡ “እስኪ አንዴ ቆይ፡ ቆይ አንዴ፡ እስኪ ትንሽ ጠብቀኝ፡ አሁን ማየት እችል እንደሆነ ልሞክር። ለብዙ ዓመታት፡ እጆቼን አይቼ አላውቅም። ላያቸው እችል እንደሆነ ልይ። ገና ምንም አላየሁም።” ኢየሱስ፡ “እምነትህ አድኖሃል” ሲለው፡ ያ በቂ ነበር። የፈለገውም ያንን ብቻ ነበር።

119 መጣበብ የሚያዝ የሚጨበጥ ነገር ፈለገ፡ የሚያዝ የሚጨበጠውም ነገር፡ ምንም ያህል የደከመ ቢሆንም እንኳ፡ ተቀባይነት አገኘ፡ ወዲያውኑ አመነው፡ ምክንያቱም መጣበብ ሲበዛ እምነት ያን ጊዜ በረታ። አያችሁ? በዚያም ፍቅር ከሱ ጋር በመቀላቀል ወደ ፍጻሜ አመጣው። መጣበብ ይህንን አደረገ።

ዕውሩ በርጤሜዎስ ራእዩን በፍጥነት ተረዳው።

120 ጴጥሮስ፡ በአንድ ምሽት በባሕሩ ላይ፡ በመጣበብ ውስጥ በገባ ጊዜ፡ እጅግ ተጨንቆ ነበር። እርሱም መጮኽ ጀመረ፡ “የሆነ ችግር አለ። ምትሃት፡ ወደ እኔ እየተራመደ ሲመጣ አያለሁ!” መርከቢቱ ልትሰምጥ ተቃርባ ነበር። እርሱም፡ “ጌታ ሆይ፡ አንተ ከሆንክ፡ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ” አለ። እርሱም ከመርከቢቱ ወርዶ መሄድ ጀመረ፥ በጀመረም ጊዜ ፈራ፡ መስመጥም ጀመረ፡ እንዲሁም መጣበብ… ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመከተል ሲሞክር፡ ስህተት ቢሰራም፡… ቤተክርስቲያን ይህንን እንደምትረዳ ተስፋ አደርጋለሁ። ሰውየው እግዚአብሔር እንዲያደርግ የነገረውን እያደረገ ነበር።

121 አሁን፡ እናንተ ክርስቲያኖች ዛሬ ማታ፡ የመንፈስ ቅዱስን መሪነት ለመከተል እየሞከራችሁ፡ በግዳጅ መሰመር ላይ ናችሁ፥ ካንሰርም ያዛችሁ፡ ወይም ሞ—ሞት ያዛችሁ፡ ካንሰር፡ የሳንባ ነቀርሳ፡ ምንም ይሁን ምን ያዛችሁ። ለተልዕኮ በምትወጡበት ጊዜ፡ ጴጥሮስ የነበረው ተመሳሳይ መብት አላችሁ።

“ጌታ ሆይ፡ አድነኝ፡ አለዚያ እጠፋለሁ።” በመጣበብ ውስጥ ሆኖ ጮኸ፡ እጁንም ዘርግቶ አነሳው። እናንተም ተመሳሳይ ነገር አላችሁ። ነገር ግን እርሱ፡ “ጌታ ሆይ፡ አድነኝ” ብሎ ጮኸ!

ተስፋ የቆረጠ ጩኸቴን ሰማ፡
ከውኃውም አነሣኝ፡ አሁን ደህና ነኝ። (አያችሁ? )

122 ይኼው ነው፡ ስትጮኹ!

123 ምናልባት ይህች ሴት፡ እናት፡ ለእርሷ ምንም ይሁን ምን፡ ትንሽ ልጅ፡ ወይም የልጅ ልጅ፡ ወይም የወንድም ወይም የእህት ልጅ፡ ማንም ይሁን ማን፡ በመጣበብ ጮኸች። እግዚአብሔር ሰማ።

124 ከዚያም በመስመጥ ውስጥ እያለ፡ እግዚአብሔር እንደሰማው፡ እናገኛለን። በግዳጅ መሰመር ላይ እያለ፡ መስመጥ ጀመረ። ወድቆ ነበር። ምንም እንኳን ብትወድቁ፡ ያ ከጉዳዩ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ሁላችንም እንወድቃለን። ከመጀመሪያው፡ ወዳቂዎች ነን። ነገር ግን አሁን ሊደርስልንና፡ ከውኃው በላይ ሊያወጣን የሚችል በብርቱ እጅ የቆመ አንድ ሰው አለን።

125 ስህተት ሰርታችሁ ከሆነ፡ አንዲት ሴት ስህተት ሰርታ ከሆነ፡ አንድ ወንድ ስህተት ሰርቶ ከሆነ፡ አንድ ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ ስህተት ሰርተው ከሆነ፥ አትስመጡ። በመጣበብ ውስጥ ሆናችሁ፡ "ጌታ ሆይ፡ አድነኝ፡ አለዚያ እጠፋለሁ፡" ብላችሁ ጩኹ! ስለ ጉዳዩ በመጣበብ ውስጥ ግቡ። እግዚአብሔር ይሰማችኋል። እርሱ ሁልጊዜ በመጣበብ ውስጥ ያለችን ነፍስ ይሰማል። ልነግራችሁ እየሞከርኩ ያለሁትም ይህንኑ ነው።

126 ውዱ ጌታችን ኢየሱስ፡ እሱ ራሱ፡ በዓለማችን ታላቁ የውጊያ አውድማ በሆነችው፡ በጌቴሴማኒ፡ በከፍተኛ መጣበብ ውስጥ ሆኖ፡ ጮኸ። የዓለምን ኃጢአት መሸከም ነበረበት፡ ወይንስ ማድረግ ይፈልገው እንደነበረው፡ ከሚወዳቸው ደቀ መዛሙርቱ ጋር በምድር ላይ ዝም ብሎ መቆየት ነበረበት? ነገር ግን ራሱን ሲያዋርድ ትህትናውን ተመልከቱ፡ "የእኔ ፈቃድ ሳይሆን ያንተ ፈቃድ ይሁን" በማለት፡ የሰማይ አምላክ ለገባው የተሰፋ ቃል፡ ለቃሉ ራሱን አዋረደ።

አስተውሉ፡ ከዚያም፡ ጥቂት ወደ ፊት ሄደ። እርሱም ጥቂት ወደ ፊት ከሄደ፡ እኛ ምን ያህል ይበልጥ ጥቂት ወደ ፊት መሄድ ይገባን ይሆን። አያችሁ? አስተውሉም፡ እዚህ ሉቃስ ውስጥ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ አጥብቆ እንደጸለየ ይናገራል። ወንድሜ፡ እህቴ፡ ኢየሱስ አጥብቆ መጸለይ ካስፈለገው፡ እኛ ምን ያህል ይበልጥ አጥብቀን መጸለይ ይኖርብናል! ክርስቶስ፡ የሰማይ አምላክ፡ ስጋን ለብሶ፡ አጥብቆ መጸለይ ካስፈለገው፡ ታዲያ በጸጋ የዳንን ኃጢአተኞች የሆንን እኛ፡ ምን ያህል ይበልጥ፡ አጥብቀን መጸለይ ይኖርብናል! ያ—ያ ውሳኔ የእግዚአብሔርን ልጅ በመጣበብ ውስጥ ከጣለው፡ እናንተንና እኔን ምን ያደርገን ይሆን? በመጣበብ ውስጥ ሆነን መጮኽ አለብን።

127 እግዚአብሔር፡ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት፡ በታላላቅ ምልክቶቹና በኃይሉ፡ ራሱን ለእኛ መግለጡ፡ በመጣበብ ውስጥ እንድንሆን ሊያደርገን ይገባል። በትክክል። እኛን ለመፈወስና ለማዳን ያለው ፈቃደኝነቱ፡ ወደዚያኛው የፈውስ ዓለት ለመድረስ ሁላችንንም በመጣበብ ውስጥ ሊጥለን ይገባል። በትክክል።

128 ተመልከቱ፡ ፍሎረንስ ናይቲንጌል... የቀይ መስቀልን መስራች የሚች ፍሎረንስ ናይቲንጌል የልጅ-ልጅ ልጅ። ፎቶዋን መጽሐፍ ውስጥ አይታችኋል፡ ክብደቷ ሠላሳ ፓውንድ ገደማ ነበር። ካንሰር በልቷት ነበር። ለንደን፡ እንግሊዝ ውስጥ፥ ከአፍሪካ፡ ወደ ለንደን፡ እንግሊዝ አምጥተዋት ነበር። እዚያም በመጣበብ ውስጥ ሆና... ወንድም ቦስዎርዝ በደብዳቤ መለሰላትና፡ "ወደ አፍሪካ መምጣት አንችልም፡" አላት።

129 እርሷም መልሳ ጻፈች፡ ነርሷ እንድትጽፍላት አድርጋ እንዲህ አለች፡ "መንቀሳቀስ አልችልም። አልችልም።"

ፎቶውንም አሳየች። ፎቶውን አይታችኋል። ከላይ ትንሸዬ ቁራጭ ነገር ማድረግ ብቻ ነበረብን። በዙሪያው ትንሸዬ ጨርቅ ብቻ ለብሳ ነበር። መጽሐፍ ውስጥ ሳስቀምጠው፡ ምናልባት አንድ ሰው፡ ሰውነቷ በጣም ስለተገለጠ... ይነቅፍ ይሆናል ብዬ አሰብኩ፡ ስለዚህ... **እዚህ** አካባቢ ትንሽ ነገር አለበስናት። በወገቧ አካባቢ ብቻ፡ ት—ትንሽ ፎጣ፡ ጨርቅ ነገር ብቻ ለብሳ ነበር። ከላይ ግን፡ ምንም አልነበረም። እንዲያውም... በዚያም ላይ ትንሸዬ የወረቀት ቁራጭ አድርገን ፎቶ ብናነሳው ብለን አሰብን... ያንን ፎቶ አነሳነው። በአጥንቶቿ

ውስጥ ትክክለኛውን የአስተሳሰብ አቋም የሌላቸው ሰዎች፥ ይህም ያንን ፎቶ በጋዜጣ ላይ በማውጣቴ እንዳይነቅፉኝ ያደርጋል።

130 ከዚያም ዶክተሩ መንቀሳቀስ እንደማትችል ሲናገር፥ እኔም እንግሊዝን ልጎበኝ እንደሆነ ስታውቅ፥ በቃሬዛ ላይ እንዲያደርጓት፥ አውሮፕላን ላይ ጭነውም ወደ ለንደን፥ እንግሊዝ፥ እንዲያመጧት አደረገች፥ ወደ በኪንግሃም ቤተመንግስት ከመውረዴ በፊትም ወደ አውሮፕላኑ ጠባቂ ልካ፥ መጥቼ እንድጸልይላት ጠባቂ ወደዚያ ላከች። እኔን ማነጋገር እስከማትችልበት ደረጃ ድረስ እጅግ ተዳክማ ነበር። በእጄ ላይ ለማስቀመጥ እጆቿን ማንሳት ነበረባቸው።

131 ለንደን እንዴት እንደሆነች ታውቃላችሁ፥ ከእናንተ መካከል አንዳንዶቻችሁ ወታደሮች እዚያ ነበራችሁ። ሁልጊዜም በጣም ጭጋጋማ ነው። እኔም እዚያ መሰኮት አጠገብ ተንበረከኩ፥ እርሷም...

እንባዋ ይፈስ ነበር። እርሷም... እንባዋ እንዲወጣ በቂ እርጥበት እንዴት እንዳገኘች አላውቅም። ከአጥንትና፥ ከቆዳ በስተቀር ሌላ ምንም አልነበረም፥ እ—እግሮቿም እዚህ ዳሌዋ ጋር፥ ለእኔ እንደሚታየኝ፥ ከሁለት፥ ወይም ሶስት ኢንች የሚበልጥ አልነበረም። ደም ስሮቿ ተጣብቀው ነበር። እንዴት በሕይወት እንደቆየች፥ አላውቅም። ፎቶዋን በኋላ አይታችኋል።

132 አልጋው አጠገብ ተንበረከኩ። አሁን፥ እርሷ በመጣበብ ውስጥ ነበረች፥ መምጣት ብችልም ባልችልም፥ ያም ሆነ ይህ፥ ሊያመጧት ነው። እኔም እዚያ ስንበረከክ፥ የዚያች ምስኪን፥ ትንሽ፥ በሞት ላይ ያለች ፍጡር እምነት፥ ልቤን-በውስጤ አደማው፥ በሙሉ ልቤም ጸለይኩ። መጸለይም ስጀምር፥ አንዲት ትንሽ ርግብ መጥታ፥ መስኮቱ ላይ አረፈች፥ እያዜመችም፥ ወደ ላይና ወደ ታች መሄድ ጀመረች። ቤት የሚያሳድጓት መስሎኝ ነበር። እንግሊዝ ከገባሁ ገና አንድ ሰዓት ገደማ ነበር፥ ልክ ከዚያ ከአውሮፕላን ማረፊያ እየመጣሁ ነበር። ስለዚህ ቤት የሚያሳድጓት መስሎኝ ነበር። ቀና ብዬም፥ “አሜን፥” ስል፥ በራ ሄደች።

ወንድሞችንም ያችን ርግብ፥ ሰምተዋት እንደሆነ ልጠይቃቸው ጀመርኩ። እነርሱም ስለ እሷ እያወሩ ነበር፥ እኔም፥ “ያች ርግብ ምን ማለት እንደሆነ አያችሁ፥” ማለት ስጀምር... እንዲህ የሚል ወጣ፥ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፥ በሕይወት ትኖሪያለሽ እንጂ አትሞችም።”

ዛሬም በሕይወት አለች። ለምን? መጣበብ። መጣበብ ሴትዮዋም ወይ መኖር ወይ መሞት፥ አቋም እንድትወሰድ ገፋፋት። መጣበብ እኔ በደረስኩበት ሰዓት እርሷም እዚያ እንድትደርስ አዘጋጀው። ከእግዚአብሔር የሆነ ምልክት፥ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** የሚለውን ለመስጠት፥ ርግብን ላከ። መጣበብ!

133 እህት፥ አሮጊቷ የፊኒክስ፥ የአሪዞናዋ ሃቲ ዋልድሮፕ፥ በመጀመሪያው ስብሰባዬ ላይ፥ በእግረኞች መንገድ ላይ እየመጣች ነበር። ኢንተርኑና ባለቤቷ እያመጧት ነበር፥ የልብ ካንሰር ነበረባት። ወደ ስብሰባው ስፍራ ለመድረስ በመሞከር፥ አቋሟን ወስዳ ነበር፥ ነገር ግን እጅግ በጣም ታማ ስለነበር... ከእንግዲህ መተንፈስ አልቻለችም ነበር፥ ካንሰሩ ልቧን በበላበት ስፍራ ደሙ ወደ ኋላ ይመለስ ነበር። አሁን፥ የልብ ካንሰር! ያም ከአስራ ሰምንት፥ አስራ

ዘጠኝ ዓመታት በፊት፡ ምናልባትም ሃያ ዓመታት ገደማ ይሆናል፡ የሆነው በ1947 ነበር።

134 አሁን፡ ለባሏና ለሀኪሙ፡ "በዚህ መሰመር ውስጥ ብሞት እንኳ፡ ወደዚያ ውሰዱኝ" አለች። መጣበብ። ራሷን ሳተች። የሞተች አይመስለኝም፥ እርሷ ግን እንደሞተች ተናግራለች። አሁን፡ ሞታ ልትሆንም ትችላለች። ይህን ካሴት ትሰማው ይሆናል፡ አያችሁ። አሁን እ—እ—እኔ... እርሷ፡ እንደሞተች ተናግራለች፥ አላውቅም። እነርሱም፡ "በመሰመሩ ውስጥ የምትመጣ አንዲት የሞተች ሴት አለች" አሉኝ። ሴትዮዋም በደረስች ጊዜ፡ ሕይወት አልባ ነበረች። ወደዚያ ባመጧትም ጊዜ፡ የጌታ ቃል መጣ፥ እኔም ሄጄ እጆቼን ጫንኩባት፡ እርሷም ተነስታ እየተራመደች፡ ወደ ቤቷ ሄደች። ይህ ከሆነ፡ በእርግጠኝነት፡ ልናገር እችላለሁ፡ አሰራ ሰምንት ዓመታት ገደማ አልፎታል፡ አሁንም ጤናማና ብርቱ ነች... ወደዚያ ሰወርድ ቱክሰን ላይ እኔን ለማግኘት ትመጣለች። መጣበብ፡ "በመንገድ ላይ ብሞት እንኳ፡ አሁንም፡ እዚያ አድርሱኝ። ሌሎችን ፈውሷል፡ እኔንም ይፈውሰኛል" አለች። ፈቃደኝነት!

135 በዚህ ቀን ልባችን በፍቅር ይሞላ፡ ትጉሃንም እንሁን፡ እንዲሁም በመጣበብ ውስጥ እንሁን። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጊዜው ሊያልፍ ይችላል።

136 ኢያኢሮሰ በአንድ ወቅት ልትሞት የተቃረበች አንዲት ትንሽ ሴት ልጅ ነበረችው። እርሱ በድንበር ላይ ያለ አማኝ ነበር። በኢየሱስ ያምን ነበር፡ ሆኖም ከምኩራብ ስለሚያሰወጡት፡ ይህንን ለመመሰከር ፈርቶ ነበር። ሆኖም ሐኪሙ አንድ ቀን ጧት መጣና፡ "አሁን እየሞተች ነው፡" አለው። መጣበብ ገባ። በነበረው ሥልጣን፡ ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር መታየት፡ ለእርሱ አዋጭ አልነበረም፡ ምክንያቱም የካህንነት ሥልጣኑን ያጣ ነበርና።

ሆኖም እላችኋለሁ፡ ድንገተኛ አደጋ ሲመጣ፡ ወደ መጣበብ ውስጥ ጣለው። ትንሿን የሰባኪ ኮቱንና ባርኔጣውን ሲፈልግና፡ ሲለብሰው ይታየኛል። እዚህም በህዝቡ መካከል፡ እየተጋፋ መጣ፥ አንዲት ሴት ልብሱን የነካችበት ሰፍራና፡ የመሳሰሉት በነበሩበት፡ ሁሉም ይጮኹ ነበር። ሆኖም ወደ ውሰጥ ገብቶ እንዲህ አለ፡ "መምህር ሆይ፡ ትንሿ ልጄ በሞት አፋፍ ላይ ተኝታለች። መምህር ሆይ፡ መምህር፡ ትንሿ ልጄ በሞት አፋፍ ላይ ተኝታለች፡ መጥተህ እጆችህን ብትጭንባት ግን፡ በሕይወት ትኖራለች" አለ። ኦህ፡ ማይ! መጣበብ አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን እንድትናገሩ ያደርጋችኋል፡ ነገሮችንም እንድታደርጉ ያደርጋችኋል። ወደ ተግባር ያሰገባችኋል። ልጁም የዳነችው በመጣበብ ነበር።

137 ደም ይፈሳት እንደነበረችው እንደዚያች ትንሽ ሴት፡ በመጣበብ ውስጥ እንሁን። መጽሐፍ ቅዱስ ገንዘቧን ሁሉ፡ በሐኪሞች ላይ እንደጨረሰች፡ ሆኖም ሊረዷት እንዳልቻሉ ይናገራል። የወር አበባ ማቋረጫ ጊዜዋ ሲደርሰ፡ መፍሰሰ ጀምሮ ነበር፡ የደም መፍሰሰ፡ ሊቆምም አልቻለም። ምናልባትም ማሳቸውን፡ በቅሎዎቻቸውን፡ ፈረሶቻቸውንና፡ የነበራቸውን ማናቸውንም ነገር ሸጠው ይሆናል፥ ሆኖም ሊረዳት የቻለ ምንም ነገር አልነበረም። ካህናቶቻቸውም ወደ እንደዚህ ዓይነት ሰፍራ ፈጽሞ እንዳትሄድ ነግረዋት ነበር። ሆኖም አንድ ጧት ወደ ታች ተመለከተች። እርሷም ማሳዋ ባለበት፡ አፋፍ ላይ ትኖር ነበር፡ እዚያም ታች በአንድ ሰው ዙሪያ ብዙ ህዝብ ተሰብሰቦ አየችና፡ "ያ ምንድነው፡" አለች?

"ያ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፡" አሏት። መጣበብ ገባ።

እርሷም፡ “እኔ እንደው እምነት ነኝ። እ—እኔ... ሆኖም የልብሱን ጫፍ ብቻ መነካት ከቻልኩ፡ እድናለሁ” አለች። እያንዳንዱንም ነቃፊና ሌላውንም ነገር ሁሉ አልፋ ሄደች። ዳሩ ግን እዚያ ቦታ ላይ ስትደርስ፡ በመጣበብ ውስጥ ሆና፡ ልብሱን ነካች።

እርሷም ያንን ስታደርግ፡ እርሱም ዘወር ብሎ፡ “ማን ነካኝ” አለ? ሁሉም ካዱ። ሆኖም እርሱ ዙሪያውን ተመለከተ። ታላቅ የእግዚአብሔር ስጦታ ነበረው። እርሱ እግዚአብሔር ነበር፥ ያቺንም ምስኪን ሴት አገኛትና የደም መፍሰሷ እንደቆመ ነገራት። ያንን እንድታደርግ የገፋፋት መጣበብ ነበር።

138 የደቡብ ንግሥትን የ—የገፋፋት መጣበብ ነበር። የእግዚአብሔር ስጦታ በሰሎሞን በኩል እየሰራ እንደነበር ሰምታ ነበር። ወደዚያ የገፋፋት መጣበብ ነበር።

139 በመጣበብ! የሰው ልጆች ናቸው፡ እንደ እናንተ፡ እንደ እኔ። ከእናንተና ከእኔ ምንም የተለዩ አልነበሩም። አምስት የስሜት ህዋሳት ነበሯቸው። ልክ እንደ እኛ፡ ይበላሉ፡ ይጠጣሉም፡ ወዘተ፡ ይኖራሉ ይሞታሉም። የሰው ልጆች ነበሩ።

140 የመንግሥቷን ከፍላ እስክትወሰድ ድረስ ወደ እጅግ ታላቅ መጣበብ ውስጥ ገፋፋት። በበረሃው ላይ ሊዘርፏት ስለሚችሉት እስማኤላውያን፡ በሰሃራ በረሃ አቋርጣ በግመል ጀርባ ላይ ስለምታደርገው የዘጠና ቀናት ጉዞዋ እንዳታስብ ወደ አንድ ሰፍራ ገፋፋት። መጣበብ! ያም ሆነ ይህ፡ ቀጠለች። እዚያም በደረሰች ጊዜ፡ ከሰሎሞን የተደበቀ ምንም ነገር አልነበረም እርሷ ማወቅ የፈለገቻቸውን ነገሮች ሁሉ ነገራት እንጂ። መጣበብ! ኢየሱስ፡ “እርሷ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ትነሳለች፡ ትፈርድበታለችም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለና” አለ። መጣበብ!

141 በማጠቃለያ ይህን ልናገር እችላለሁ። በቅርብ ጊዜ፡ ወደ ሜክሲኮ ወረድ ብሎ፡ አንድ የሚያጣብብ ነገር አየሁ። እዚያ ትልቅ አውድማ ውስጥ፡ ወደ መድረኩ ገና መድረሴ ነበር፡ ህዝቡም ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ እዚያው ነበሩ፡ ጊዜውም ወደ ማታው አራት ሰዓት ተቃርቦ ነበር። ከዚያ ምሽት በፊት፡ ከሰላሳ ዓመታት ገደማ ጀምሮ፡ ሙሉ በሙሉ ዕውር የነበረ አንድ አዛውንት፡ አይኑ በርቶለት ነበር፡ በዚያም ቀን፡ እየመሰከረ በከተማዋ ውስጥ ይዘዋወር ነበር። ምናልባት ሰላሳ፡ አርባ ያርድ በሚያህል ርቀት የተዘረጋ፡ ያረጁ ልብሶች ክምር፡ ያን **ያህል** ከፍታ ያለው፡ ያረጁ ሻሾች ብቻ ነበሩ። ምናልባትም አርባ፡ አምሳ ሺህ ህዝብ በዚያ ነበረ። ያረጁ ባርኔጣዎችና ሻሾችም የነማን እንደሆኑ፡ በመካከላቸው መወሰን የነበረባቸው ይመስለኛል። ዝናቡም ዶፍ ያወርድ ነበር።

142 በግንቡ፡ በገመድ አወረዱኝ፡ ወደ መድረኩም ወጣሁ። አገልጋዩ... እዚህ የተቀመጠውን ሰው፡ አመጡት... እሱና ልጁ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ከሚቺጋን መጥተው፡ ስለ ወንድም አርመንት አወሩ። እዚህ እናስታውሰዋለን። ዛሬ ማታ በክብር ጎዳናዎች ላይ ይገኛል። ወንድም አርመንት እዚያ ነበር፡ ኮቱንም አውልቆ፡ በዝናቡ ውስጥ ቆሞ፡ ጃክ ይንቀጠቀጥ ስለነበር፡ ወንድም ጃክ ሙር እንዲለብሰው ሰጠው። ያ የደቡብ ሰው በሜክሲኮ በነበረው ቀዝቃዛ ዝናብ በረዶ ሊሆን ተቃርቦ ነበር። በዚያም ቆሞ ነበር።

143 ልጄ፡ ቢሊ፣ ፖልም ወደ አጠገቤ መጥቶ፡ እንዲህ አለኝ፡ “አባዬ፡ የሆነ ነገር ማድረግ አለብህ። በዛሬው ጠዋት የሞተባትን ህጻን ይዛ የመጣች አንዲት ትንሽ ሜክሲኳዊት ሴት እዚያ ታች አለች። ከሰልፉ ውስጥ እንድትወጣ አድርገው ሊይዟት የሚችሉ በቂ አሸሮች የሉኝም” አለኝ። በዚያ ዓይነ ሰውር ላይ እጅ መጫን እይታውን ከሰጠው፡ በሞተው ህጻን ላይ እጅ መጫንም ህይወቱን ይሰጠዋል። ካቶሊክ ነበረች። እሷም፡ ሊያሰቆሟትም፡ አልቻሉም።

ወንድም ኤስፒኖዛና ሌሎችም፡ “ተጨማሪ የጸሎት ካርዶች የሉንም። እስከ ሌላ ምሽት መጠበቅ አለብሽ” ብለዋት ነበር።

144 እሷም፡ “ልጄ ሞቷል። ጠዋት እንደሞተ ነው። ወደዚያ መግባት አለብኝ” አለች። የጸሎት ካርድ ቢኖራትም ባይኖራትም፡ እየመጣች ነበር። በዚያም ወደ ሦስት መቶ የሚጠጉ አስተናጋጆች ተሰልፈው ነበር። እርሷም በእግሮቻቸው ስር ሾልካ ትገባለች፡ በጀርባቸውም ላይ ዘላ ትወጣለች፡ ይህንም የሞተ ህፃን ይዛ ትሮጣለች፡ በመካከላቸውም ትወድቃለች። ይህ ለእርሷ ምንም አልነበረም፥ ጥረቷ እዚያ ለመድረስ ነበርና። በመጣበብ ነበረች። እግዚአብሔር በልቧ ውስጥ፡ ይህ፡ “አይንን ያበራ አምላክ፡ ህይወትንም መስጠት ይችላል” ብሎ ተናግሯታል። ኦህ፡ ማይ! በመጣበብ ውስጥ ነበረች። በውስጧ የሆነ ነገር ይቀጣጠል ነበር።

145 ኦህ፡ የታመማችሁ ሰዎች፡ ያ ነገር ለጥቂት ደቂቃዎች በውስጣችሁ እንዲቀጣጠል ብትፈቅዱና፡ ምን እንደሚፈጠር ተመልከቱ፡ ያ ዓይነቱ መጣበብ ነው። በቀደም ምሽት ይህንን ትንሽ ልጅ መፈወስ የቻለው አምላክ፡ ያቺን ካንሰር ያለባትን ሴት መፈወስ ይችላል፡ ይህንንም ሰው መፈወስ ይችላል፡ ይህንንም ማድረግ ይችላል፡ ሚሰ ፍሎረንስ ናይቲንጌልን፡ ኦህ፡ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩትን! እርሱ፡ ያ፡ አከራካሪ ያልሆነ ማስረጃ ነው፥ ሙታንን ማስነሳት፡ በሽተኞችን መፈወስ፡ እንዲሁም ሌላውም ነገር ሁሉ ማድረግ ይችላል። አምላክ ከሆነ፡ ያንን ማድረግ ይችላል፥ ትናንት አምላክ ነው፡ ዛሬም አምላክ ነው። በመጣበብ ውስጥ ሁኑ፡ ያኔ የሆነ ነገር ይሆንላችኋል።

146 ከዚያም፡ በዚያ መጣበብ ውስጥ፡ መገፋፋቷን ቀጠለች። ለወንድም ጃክ ሙር፡ እንዲህ አልኩት፡ “አታውቀኝም። አይታኝም አታውቅም። እዚህ መድረክ ላይ ያለው ማን እንደሆነ አታውቅም። አሁን ያቺ ካቶሊክ ሴት፡ እንግዲህ፡ አንዲትም የእንግሊዝኛ ቃል መናገር አትችልም፡ ታዲያ ማን እንደሆነ እንዴት አወቀች? ” በመቀጠልም፡ “ወደ ታች ውረድና፡ ለህጻኑ ጸልይለት፡ ያም ያረካታል፡ መንገዷንም ትቀጥላለች” አልኩት። እንዲህ አልኩ፡ “ችግር አይፈጥርም... ” እዚያ ታች የማያቋርጥ ጩኸት ነበር። ዘላ ትነሳለች፡ ሁሉም ይጮኻል። በትከሻዎቻቸው ላይ እየሮጠች፡ በመካከላቸው ትወድቅ ነበር። ትንሽ ወደፊት ለመምጣት ትሞክራለች፡ ከዚያም መልሰው ሊያሰወጧት ይሞክራሉ፥ ዳሩ ግን ይህን ህጻን ይዛ፡ አስተናጋጆችንና ሌላውንም ነገር ሁሉ እያተራመሰች፡ በእግሮቻቸው መሃል ትመጣ ነበር። ለእሷ ምንም ለውጥ አላመጣም፥ ወደዚያ እየወጣች ነበር። እዚያ መድረስ ነበረባት! ምንም ቢሆን ለውጥ አያመጣም፡ ወደዚያ መድረሷ አይቀርም ነበር። አገልጋዩ...

147 ታዲያ ይህ ልክ እንደ ሱነማዊቷ ሴት ታሪክ አይደለምን? ሆኖም፡ ያ የሆነው ከሠላሳ-አምስት መቶ ዓመታት በፊት አልነበረም። ያ የሆነው ከሦስት ወይም

አራት ዓመታት በፊት ነበር። አያችሁ?

ዛሬ ማታም ያው ተመሳሳይ ነገር ሊሆን ይችላል። ያው ተመሳሳይ መጣበብ ሲነሳ፡ የፈለጋችሁትን እንድትቀበሉ፡ ፍቅርንና እምነትን ወደ ውጊያው ግንባር ይጥላችኋል፡ ምክንያቱም ልታገኙት እንደምትችሉ የእግዚአብሔር ተስፋ ነውና። ያ በትክክል እውነት ነው።

148 ዞር አልኩ፥ በቦታውም እኔ፡ አገልጋዩ፡ ወይም ወንጌላዊው ነበርን። ዞር አልኩ። ለሴትዮዋ አዘንኩላት፡ ነገር ግን ምንም መጣበብ አልነበረም። አያችሁ? ዞር ብዬ፡ "መልካም፡ ወንድም ጃክ ይጸልይላታል፥ ያ—ያም እልባት ያስገኝላታል" ብዬ አሰብኩ። ዞር አልኩ። እንዲህ አልኩ፡ "አሁን እየተናገርኩ እንደነበረው፡ እምነት... "

ወደዚያም ስመለከት፡ ራዕይ መጣ። አንድ ትንሽ ህጻን እዚያ ተቀምጦ አየሁ፡ ጥርስ የሌለው፡ ጥቁር-ፊት ያለው ትንሽ የሜክሲኮ ህጻን። እዚያ ተቀምጦ፡ ይስቅልኝ ነበር። "አንድ ደቂቃ። አንድ ደቂቃ፡" አልኩ። የእርሷ መጣበብ መንፈስ ቅዱስ ርዕሴን እንዲቀይር፡ ዓይኖቼን እንዲቀይርና የእሷን ልጅ እዚያ ተቀምጦ እንዲያሳየኝ አደረገው። ያም መንፈስን መለሰው። "አንድ ደቂቃ። አንድ ደቂቃ ቆዩ። ህጻኑን አምጡልኝ፡" አልኩ።

እርጥብ፡ በውሃ የራስ፡ ሰማያዊና ነጭ ብርድ ልብስ፡ **ያን** ያህል ርዝመት ያለው፡ ትንሽ የሞተ አካል፡ ይዛ መጣች። በእጇ መስቀል ይዛ፡ ወይም መቁጠሪያ ይዛ፡ እነዚያን "ውዳሴ ማርያም፡" ለማለት ወደቀች። "አስቀምጪው፡ ያ አስፈላጊ አይደለም፡" አልኳት።

ወደነበርኩበት ተጠጋችና፡ "ፓድሬ፡" እያለች ትጮህ ነበር፡ ትርጉሙም "አባት፡" ማለት ነው።

"እንደዛ አትበይ። እንደዛ አትበይ። ታምኛለሽን፡" አልኳት? እሱም በስፓኒሽ ቋንቋ፡ ታምን እንደሆነ ጠየቃት።

"አዎን፡" ታምናለች። እንዴት ማመን እንደቻለች ጠየቃት። እርሷም፡ "እግዚአብሔር ለዚያ ሽማግሌ አይኑን ማብራት ከቻለ፡ ለልጄ ህይወትን ሊሰጠው ይችላል" አለች። አሜን። መጣበብ ወደዚያ ገፋፋት። በእኔ በኩል ምንም አልነበረም፥ ራዕይ ብቻ ነው ያየሁት።

"ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ የአንድን ትንሽ ህጻን ራዕይ አይቻለሁ፡ ምናልባት ይህኛው ሊሆን ይችላል፡" አልኩ።

በዚያን ጊዜ እግሮቹን አፈራገጠ፡ "ዋ! ዋ! ዋ፡" አለ!

"ወደ ሐኪሙ አብራችኋት ሂዱ። ከሐኪሙም 'ህጻኑ ሞቷል፡' የሚል የጽሁፍ መግለጫ አምጡ፡" አልኩ። እናም... ሐኪሙም ጻፈላቸው፡ "የዚህ ህጻን ትንፋሽ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ሦስት ሰዓት ላይ በቢሮዬ ውስጥ ልብ ምቱ ቆሟል፡ በከፍተኛ የሳንባ ምች ሞቷል" የሚል መግለጫ ጻፈ። ኦህ፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ ህጻኑ ዛሬ ማታ በሜክሲኮ በህይወት እየኖረ ነው። ለምን? መጣበብ በዚያች ምስኪን እናት ልብ ውስጥ ገባ፡ ለትንሹ ልጇ ስታለቅስለት ነበር፡ እግዚአብሔር... የሰውን ዓይነ ሰውር ዓይኖች ሲፈውስ አይታ፡ የሞተውን ህጻን ማስነሳት እንደሚችል አወቀች።

149 መጣበብ! "በፍጹም ልባችሁ ስትፈልጉኝ፡ ያኔ እሰማችኋለሁ።" አያችሁ?

150 መንግስቱ! “ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ድረስ ነበሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ የእግዚአብሔር መንግስት ይሰበካል፡ ሰውም ወደዚያ በኃይል ይገባል።” ዝም ብላችሁ ቆማችሁ፡ “ጌታ ሆይ፡ በእንገትጌዬ እንሳኝ፡ ወደ ውስጥ ግፋኝ” አትሉም። ወደ ውስጥ በኃይል ትገባላችሁ። በህይወትና በሞት መካከል በመሆን፡ በመጣበብ ውስጥ ትገባላችሁ።

151 ለሌላ ታሪክ ጊዜ ቢኖረኝ እመኛለሁ፡ አሁን እያሰብኩት የነበረው፡ የተሳሳተ መንገድ ስለወሰደች፡ አንዲት ሴት፡ ልጃገረድ፡ አዲስ ምዕራፍ እንዴት እንደጀመረችና ሌሎች ነገሮች እንዴት እንዳደረገች ስለእሷ ነው፡ እኔ እንዲህ እስከምላት ደርሳ ነበር፡ “እህቴ... ”

ተነሳችና እንዲህ አለች፡ “ደ—ደህና እንደምሆን አምናለሁ” አለች።

እንዲህ አልኳት፡ “አይ፡ አይ! እዚያው ቆይ።”

ከዚያም፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ ትንሽ መጸለይ ጀመረች፡ ቀጥሎም ድምጿን ከፍ እያደረገች መጣች። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ተጣበበች፡ እንዲህም አለች፡ “አምላክ ሆይ፡ አድነኝ!”

152 የአልኮል ሱሰኞች ማገገሚያ ሊፈውሰው አልቻለም። ሌላ ምንም ሊያደርገው አልቻለም። ነገር ግን እነዚያ ትልልቅ፡ ጥቁር ዓይኖች ተመለከቱኝ፡ እንባዋም በጉንጮቿ ላይ ይፈስ ነበር፥ እንዲህ አለች፡ “አንድ ነገር ሆኗል።” ኦህ፡ አዎን! አዎ፡ ወዳጄ! አንድ ነገር ሆኗል። ተጣበበች።

153 እስቲ ስለዚህ ነገር በሞትና በህይወት መካከል፡ እንጣበብ።

154 መጣበብ ካልቻላችሁ፡ ወደዚህ አትምጡ። ከተጣበባችሁ፡ ወደዚህ ኑና ተመልከቱ፡ እዚህ እንደደረሳችሁ ወ—ወዲያውኑ ታገኙታላችሁ።

155 እንጸልይ። በመጣበብ ውስጥ ሆናችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት ተጠባበቁ፡ በእናንተ ላይ ትመጣለች።

156 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ፡ ማረን፡ ጌታ ሆይ። በውስጣችንም መጣበብን ጀምር። አቤቱ አምላክ ሆይ፡ ማረን ብዬ፡ እጸልያለሁ፡ ህዝቡም ዛሬ ማታ በተጣበበ ልብ ይፈልጉህ። እዚህ እንዳለህ እናውቃለን፡ ጌታ ሆይ። ትላንት፡ ዛሬም፡ እስከዘላለምም ያው ነህ።

157 አሁንም ምልክቱን የያዙ እነዚህ ሰዎች፡ ከሞት ወደ ህይወት ተሻግረዋል፡ ከቀድሞ አለማዊ ህይወት ወደ አዲሱ ተለውጠዋል። አዎ ተለውጠዋል። ደሙ ተረጭቷል፥ አምላክ ሆይ፡ የምልክቱን ማረጋገጫ፡ ሰጣቸው። ያንን ምልክት በእጃቸው ይውሰዱ፡ የታመሙትም፡ እንዲህ ይበሉ፡ “የተገዛ የእግዚአብሔር ንብረት ነኝ። በክርስቶስ ውስጥ ነኝ፡ በእርሱም ዘንድ ምንም ህመም የለም። በክርስቶስ ውስጥ ነኝ፡ በእርሱም ዘንድ ምንም ኃጢአት የለም። በክርስቶስ ውስጥ ነኝ፡ በእርሱም ዘንድ ምንም አለማመን የለም። ዲያብሎስ የነገረኝን ሁሉ እክዳለሁ። የእኔ የሆነውን ምልክቴን እወስዳለሁ... ‘እርሱ ስለ መተላለፌ ቆሰለ፥ ስለ በደሌም ደቀቀ፥ የሰላሜም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቁስል ተፈወስኩ።’ እግዚአብሔር እንዳወቀኝ የሚያሳየውን ምልክት፡ አሁን ይዣለሁ፡ ያ አላማ፡ በጌታ በኢየሱስ ደም የተገዛው፡ አካል ነኝ። ሞቱን የሚያሳየውን ምልክት በእጆቼ ይዣለሁ፡ ምክንያቱም እርሱ ተነስቷል፡ የእርሱ ነኝ እርሱም የእኔ ነው። ከዚህች ሌሊት ጀምሮ፡ እግዚአብሔርን

አምናለሁ በሚል ጽኑ እምነት እሄዳለሁ፡ እዚያ ስደርስና መሰፈርቶቹን ሳሟላ፡ እፈወሳለሁ” በሉ።

ምክንያቱም፡ ከከንፈሮቹ የወጡት የመጨረሻዎቹ ቃላት፡ እነዚህ ነበሩ፡ “በድውዮች ላይ እጃቸውን ይጭናሉ፡ እነርሱም ይድናሉ።” ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። መጣበብ ይምጣ፡ በኢየሱስ ስም እጠይቀዋለሁና። አሜን።

እችላለሁ፡ ቆርጫለሁ፡ አምናለሁ፥
እችላለሁ፡ ቆርጫለሁ፡ አምናለሁ፥
እችላለሁ፡ ቆርጫለሁ፡ አምናለሁ
ኢየሱስ አሁን ፈውሶኛል።

ኦህ፡ እችላለሁ፡ ቆርጫለሁ፡ አምናለሁ፥
እችላለሁ፡ ቆርጫለሁ፡ አምናለሁ፥

አስቡት፥ “ቆርጫለሁ!”

እችላለሁ፡ ቆርጫለሁ፡ አምናለሁ
ኢየሱስ አሁን ፈውሶኛል።

158 ያንን ታምናላችሁ? “ቆርጫለሁ! በእግዚአብሔር ጸጋ፡ ቆርጫለሁ፡ ያ እንዳች ነገር እስኪመታኝ ድረስ በፍጹም አላቆምም። እጆች እንዲጫኑብኝም ወደዚያ እሄዳለሁ።”

አሁን፡ እግዚአብሔር ከቶ ጥሎን አያውቅም። ታላቁ ሀኪም አሁን ቀርቧል ብዬ አምናለሁ። ቃሉን የጻፈውን አምላክ አምናለሁ፡ መሰዋዕቱን ያደረገውን አምላክ አምናለሁ፡ ዛሬ ማታ ከሀጢያት የሚያነጻንን የእግዚአብሔርን ምልክት አምናለሁ፡ የገዛ ህይወቱ የሆነው፡ ምልክት፡ እዚህ ከእኛ ጋር ነው። “እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ። ጥቂት ጊዜ አለ አለምም ከእንግዲህ ወዲህ አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር፡ በእናንተም ውስጥ እሆናለሁና።” ያንን ታምናላችሁ? በእርሱ ታምኛለሁ። እርሱ እንደሚያደርገው አምናለሁ። አታምኑም?

159 አሁን፡ ያንን እንደጀመርኩ፡ ራእዮች ሲታዩ አያለሁ፡ አሜን፡ ታላላቅ ነገሮችን የሚናገሩ፡ የጌታ ታላላቅ ራእዮች። አሜን! ያንን ከጀመርኩ፡ ሌሊቱን ሙሉ እዚህ እንሆናለን። ልታምኑበት ነው? ታምናላችሁን? አሜን! በሙሉ ልቤ አምናለሁ።

160 እዚያ ከወንድም ፓልመር ዘንድ የተቀመጠችው ትንሽ ሴት፡ ለእኔ እንግዳ ናት። ከጆርጂያ የመጣች ናት፡ በሴቶች ህመምም እየተሰቃየች ነው። እግዚአብሔር እንደሚፈውሳት ካመነች፡ ያደርግላታል። ሴትዮዋን በህይወቴ አይቻት አላውቅም፡ ሆኖም ችግሯ ይህ ነው።

161 ያቺ ትንሽ ሴት፡ ከዚህ በፊት መልእክቱን ሰምታ እንደሆነ፡ ወይም እንዳልሆነ አላውቅም፡ ነገር ግን እዚህ እየሰበክሁ ሳለ፡ አየኋት። ብቻ እመኑትና ትክክል እንደሆነ ተመልከቱ። አሜን። ብታምኑ ብቻ! በትክክል።

162 እዚህ ጆርባ የተቀመጠችው እመቤት የጆርባ ህመም አለባት፡ በጣም እየተሰቃየች ነው፡ ስሟ ወይዘሮ ዊዝደም ነው። በፍጹም ልብሽ ካመንሽ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል። ሴትዮዋን በህይወቴ አይቻት አላውቅም፡ ነገር ግን እዚያ ተቀምጣ፡ እየተሰቃየች ነው። ቢጫ ቀሚስ ለብሳለች። ልክ ነው?

መልካም። እርስ በርሳችን እንግዶች ነን? አዎ። መልካም፡ ጌታዬ። ወደ ቤትሽ ሂጂ፡ ደህና ሁኚ። ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል። አሜን።

163 ያንን አሁን የተቀበለችው ሌላ ሴት፡ የጀርባ ህመም ያለባት፡ እዚህ ተቀምጣለች። የጀርባ ህመም አለባት። አንድ ልጅ አላት፡ እርሱም የጭንቅላት ህመም አለበት። ኧ-ህ። በትክክል። ስሟ ወይዘሮ ፓርከር ነው። በሙሉ ልብሽ እመኚ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ሁለታችሁንም ይፈውሳችኋል። አሜን! ለኔ እንግዶች ናችሁ። ይህ ፍጹም ልክ ነው። አሜን! በሙሉ ልባችሁ እመኑ።

164 እዚህ ጀርባ ከሚቺጋን የመጡ አንድ አዛውንት ሰው ተቀምጧል። በጆሮአቸው ላይ ችግር አለ። ኦህ፡ ስለ እነዚህ ድምጾች፡ መንፈሳዊ ችግር ነው ብለው ያስባሉ። ልክ ነው? ያ—ያንን እያመኑ ነው... እግዚአብሔር ይሁን፡ ወይም ማን እያነጋገሮት እንደሆነ አያውቁም። በጆሮዎ ውስጥ ጩኸት ይሰማዎታል። ለእርሶ ፈጽሞ እንግዳ ነኝ። ያ ልክ ከሆነ፡ እጆችዎን ያንሱ፡ እየሆነ ያለውም ያ ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ አይረብሾትም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውሰዎታል።

በታላቁ ሀኪም ያምናሉ?

165 ላናግሮት እችል ነበር፡ ነገር ግን፡ ከኖርዌይ፡ አይረዱኝም፥ የኖርዌይ ቋንቋ። ኧ-ህ። መልካም፡ እህቴ፡ ቋንቋውን መናገር ከቻልሽ፡ እያመኑ፡ ወደ ቤቱ እንዲሄዱ ንገሪያቸው። የጭንቅላት ህመሙ እንደሚለቃቸው ንገሪያቸው። እንግዲህ፡ እንደማላውቃቸው ታውቂያለሽ። እንዲጸለይላቸው፡ ከኖርዌይ መጥቷል። እንደዳነ ሰው፡ ይመለስ። አሜን።

166 ኦህ! “ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንት፡ ዛሬም፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው!” ምንድነው? ያ የእሳት አምድ ነው። መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በህይወት እንዳለ የሚያሳየው፡ ያ ምልክት ነው። ከረጅም ጊዜ በፊትም፡ ሰዎች፡ እነዚህን ነገሮች ሲያደርግ ባዩት ጊዜ፡ ቃሉ ስለሆነ ሀሳባቸውን አውቆ ነበር። “የእግዚአብሔርም ቃል በሁለት-በኩል ከተሳለ ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፡ የልብንም ሀሳብና ስሜት ይመረምራል።” አሜን።

167 ውሃ ሲፈስ አየሁ፡ ይህ ወጣት ልጅም ሲመጣ አየሁ። እዚያ መጽሐፍ ሰምቶ፡ አነበበና፡ በኖርዌይ ቋንቋ፡ ጻፈ። መረዳትን አግኝቷል፥ የሆነ ሰው አናግሮታል። ችግር አለበት፡ ነገር ግን፡ በሙሉ ልቡ ካመነ፡ ጌታ ኢየሱስ ይፈውሰዋል። ከሩቅ መንገድ መጥቷል፡ ያውም፡ ምስኪን ልጅ ሆኖ፡ ገብቶ ለመዳሰስ እየታገለ ነው። ከጥቂት ደቂቃ በኋላም፡ እጆቻችንን እንጭንበታለን።

168 ታምናላችሁ? አሜን! እንዴት ድንቅ ነው! ኦህ፡ ማይ! “ታላቁ ሀኪም አሁን ቀርቧል።” እህቴ፡ ያቺ እህት እንግረን የት ነች፡ ፒያኖው ላይ ያለችው ሌላኛዋ እህትስ የት ነች? ፈቃደኛ ከሆናችሁ፡ በፍጥነት መጥታችሁ፡ መዝሙሩን ስጡን፡ “ያ ታላቁ ሀኪም አሁን ቀርቧል፡ የሚራራው ኢየሱስ” የሚለውን ስጡን።

169 **በዚህ** መተላለፊያ ላይ ያላችሁና፡ እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ሰዎች፡ እባካችሁ በአንድ ጊዜ አንድ መተላለፊያ ብቻ በማድረግ፡ **ወደዚህ** በኩል ውረዱ። ወንድም ኔቪል፡ ፈቃደኛ ከሆንክ ያንን አድርግ። ወንድም ካፐስ ወይም ከነዚያ መዘምራን መሪዎች አንዱ የት አለ? ወንድም እንግረን፡ ወይም ወንድም ካፐስ፡ ወይም ሌላ ሰው፡ ወደዚህ መጥታችሁ፡ ብትዘምሩ፡ ፈቃደኛ ከሆናችሁ

ይህንን መዝሙር ብትመሩልን። ወንድም... ከነዚያ ወንድሞች አንዱ የት አለ? ጥሩ። መልካም፡ ወዳጄ፡ ያ ጥሩ ነው። መልካም። ሁሉም ሰው በጸሎት ይሁን!

170 አስታውሱ፡ መጣበብ! መጣበብ ምን እንደሚያደርግ አያችሁ? መጣበብ ባህር ያሻግራችኋል። መጣበብ ከሌላ ክልል ያመጣችኋል። መጣበብ ወደ የትኛውም ቦታ ያንቀሳቅሳችኋል። አንድ ውድ አዛውንት አባትና ልጃቸው፡ በመጣበብ፡ ወደ ውስጥ ለመግባት፡ ለመምጣትና፡ የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ፡ እንደምንም ብለው ተቀመጡ፥ ከጥቂት ጊዜያት በፊት እኔ ወደዚህ ከመግባቴ ትንሽ ቀደም ብሎ፡ መንፈስ ቅዱስ እዚህ ሰብሰባው ውስጥ ነገሩን ገለጠ። ኦህ!

ከተዘመሩት ሁሉ እጅግ ጣፋጭ መዝሙር፡
ኢየሱስ፡ የተባረከው ኢየሱስ።

ያ ታላቅ ሐኪም መጥቷል፡
መድኃኒታችን...

ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ የባሪያህን ጸሎት ሰማ፡ ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን። ለክብርህ ስትል፡ ከእነዚህ ከእያንዳንዳቸው ጋር እንድትገናኝና እንድትፈውሳቸው፡ በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ።

... የኢየሱስ ድምጽ።

በሱራፌል መዝሙር ውስጥ እጅግ ጣፋጭ ዜማ፡
በሟች አንደበት ጣፋጭ ሰም፡
ኦህ፡ ከተዘመሩት ሁሉ እጅግ ጣፋጭ መዝሙር።

አሁን የተጣበቡት፡ በእርግጥ እንደምትፈወሱ የሚያውቁት... አሰቡት፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ ካለፈው እሁድ ማታ ጀምሮ የነበሩት፡ መቶ በመቶዎቹ፡ በዚህ ሳምንት ተፈውሰዋል።

መድኃኒታችን...

171 ተመልከቱ፡ ይመጣል። አያችሁ፡ አስቀድሞ ፈውሷችኋል። ቃሉን ያመጣል፡ ያረጋግጠዋል፡ መገኘቱንም ያሳያል። ከእግዚአብሔር ውጭ ማንም እነዚህን ነገሮች ማድረግ አይችልም። ያንን ታውቃላችሁ። የመሲሑ ምልክት ነው። እኔ መሢሕ እንዳልሆንኩም ታውቃላችሁ፡ ስለዚህ እርሱ ነው። አሁን እዚህ ሁሉንም ነገር አረጋግጦላችኋል።

አሁን ወደ መጣበብ ሊያስገባችሁ ይገባል። ይህንን ሰፍራ ሊያነቃቃና ሊነካው ይገባል... አይ፡ ልክ እ—እ—እ—እንደ ክብሪት በባሩድ በርሜል ላይ ሊሆን ይገባል። በእርግጠኝነት! እምነትንም ሊያፈነዳው ይገባል፡ ፍቅርንና—መጣበብም እነዚያን ህዝብ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ እንዲገቡ ሊያደርጋቸው፡ በሙሉ ልባቸውም እንዲያምኑ ሊያደርጋቸው ይገባል። አሁን እያንዳንዳችሁ፡ ታምናላችሁ? መልካም። አሁን፡ ቢሊ፡ አንተ...

172 ቶኒ፡ ለአንድ ደቂቃ ወደዚህ ተመልከተኝ። ለረጅም ጊዜ አላየሁህም፡ ሆኖም ታመሃል። እንደ ተቅማጥ ባለ በሽታ እየተሰቃየህ ነው። ልክ ነው። ሊቆም ነው። ሊለቅህ ነው። በዚያ ማለፍ ሲጀምር፡ ያ ነገር ሲከተለው አየሁት። አሁን ከእግዚአብሔር ሊሰወር የሚችል ምንም ነገር የለም። ፈጽሞ አላየሁም... ቶኒን

ለወራት ያህል አላየሁትም፡ ብዬ እገምታለሁ፡ ሆኖም ያ እንዳለበት አይቻለሁ። ነበረበት፥ አሁን ግን የለበትም።

173 ራሶቻችንን እናጎንብስ። ማንም ዓይኑን አይግለጥ። አንድም ዓይን አይመልከት። ሁሉም ሰው በጸሎት ይሁን። ቢሊ ፖል ወይም ወንድም ኔቪል፡ እንዳቸው፡ ጊዜው ሲደርስ ቀጣዮቹን መስመሮች ይጠራል። አሁን ሁሉም ሰው በጸሎት ይሁን። አሁን ልንሞክር ነው፥ መካከለኛው መተላለፊያ ስትጠሩ ወደ ግራ-እጃችሁ በኩል ይመጣል፡ እ—እንዲሁም **እዚህ** ያለው የግራ-እጅ መተላለፊያ ስትጠሩ ወደ ግራ-እጃችሁ በኩል ይመጣል። ወንድም ኔቪል ይጠራችኋል።

አሁን፡ እነዚህ ሰዎች ሲያልፉ እጆቻቸውን ሊጭኑባቸው ከእኔ ጋር እዚህ ለመቆም የሚፈልጉ ከወንድሞች መካከል፡ እዚህ ይኖሩ ይሆን? ማናችሁም አገልጋይ ወንድሞች፡ ያንን ለማድረግ ከፈለጋችሁ መጥታችሁ ከእኔ ጋር እንድትቆሙ በእርግጥ ተጋብዛችኋል። የተነጠለ ነገር አይደለም። ልክ እንደኔ ለታመሙት የመጸለይ መብት አላችሁ።

መንፈስ ቅዱስ እዚህ እንዳለ አውቃለሁ። ያንን የማያምን ማንም ሰው ቢኖር፡ ችግር አለበት።

174 ጥሩ፡ የምንጠይቃቸውን እነዚህን ነገሮች፡ እግዚአብሔር አሁን እንደሚሰጠን በሙሉ ልባችን እንመን። አሁን እምነት ይኑራችሁ። አትጠራጠሩ።

ሁሉም ሰው፡ እርስ በርሱ ይጸልይ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን አለ? “ሀጢያታችንን እርስ በርሳችን እንናዘዝ፥ አንዱ ስለ አንዱ ይጸልይ… ”

175 በመስመሩ የምትመጡት ሰዎች፡ እነዚህ እጆች እንደነኳችሁ ወዲያውኑ፡ ስለተፈወሳችሁ ደስ እያላችሁና እግዚአብሔርን እያመሰገናችሁ ከዚህ ትወጣላችሁ።

መልካም፡ ወንድም ካፕስ መዝሙሮቹን ሲመራ አሁን ሁሉም ሰው በጸሎት ይሁን።

ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አሁን እርዳን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እያንዳንዱን ሰው እንዲነካ እጸልያለሁ፡ በሕመምተኞች ላይ እጃችንን በመጫን ትእዛዝህን ስንከተል ይፈወሱ። አንተም፡ “ይድናሉ” ብለሃልና። እናምነዋለን፡ አባት ሆይ፡ በኢየሱስ ስም። አሜን።

መልካም፡ መጸለይ ስንጀምር አሁን ሁሉም ሰው በጸሎት ይሁን። በመጀመሪያ፡ በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ያለ ትንሽ የታመመ ልጅ አለ።

እንዲፈወስ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ በልጁ ላይ እጃችን እጭናለሁ።

አዎን፡ ወዳጄ።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም… [የጸሎት መስመሩ ለአስራ ሰምንት ደቂቃዎች ቆይቷል፡ የወንድም ብራንሃም ቃላት አይለዩም—አርታዒ።]… ? …

> ከተዘመሩት ሁሉ እጅግ ጣፋጭ መዝሙር፡
> ኢየሱስ፡ ብሩክ ኢየሱስ።

176 እግዚአብሔር እንዳደረገው የምታምኑ ሰንቶቻችሁ ናችሁ፡ በልባችሁ እርግጠኛ የሆናችሁ፡ በተረጋገጠ ዋስትና፡ ቃሉን ስለታዘዛችሁ እግዚአብሔር

ጥያቄያችሁን እንደመለሰላችሁ የምታምኑ? ሆኗል። ተፈጽሟል። ተ—ተደርጓል። የተጠናቀቀ ስራ እንደሆነ፡ በሙሉ ልባችሁ እመኑት።

177 አሁን በዚህ ሳምንት ተመልከቱ፡ ዳግመኛም ስትመለሱ፡ የሆነውን ተመልከቱ።

178 በሚቀጥለው ጊዜ ስመለስ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ የጸሎት መስመሩን፡ ከነዚህ ክፍሎች በአንዱ፡ ወደዚያ ላስገባቸው ባሰብኩት ትንሽ ክፍል ውስጥ እንደማደርገው እገምታለሁ፡ አያችሁ። ዘመኑ፡ አሁን እየተገለጠ እንደሆነ አምናለሁ፡ አያችሁ።

179 ሰዎቹን አንድ በአንድ ማምጣት ወደምችልበት፡ መርምሬ እስካገኘው ድረስ ከእነርሱም ጋር በግል ወደምገናኝበት፡ ከዚያም በዚያው ጊዜ ከእነርሱ ጋር ትክክል ሆኜ እስክቆይ ድረስ፡ በዚያው መንገድ ወደምቀጥልበት፡ ደረጃ መድረስ እፈልጋለሁ።

180 እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይባርክ። እዚህ ስለነበራችሁ በጣም ደስ ብሎናል። አግኝታችኋል... ? አሁን ጸንታችኋል? እናንተ... ? በመጣበብ ውስጥ ናችሁ፡ ለፈውሳችሁ የነበራችሁ መጣበብ? እግዚአብሔር ቃል የገባውን እንደሚያደርግ በተናገረው ፍቅር፡ እምነትና መተማመን ውስጥ አሁን ያ አብቅቷልን? እግዚአብሔር ያደርጋል።

ከነዚያ ትንንሽ ልጆች መካከል፡ ዛሬ ማታ በዊልቼር ወንበር ላይ ያሉ፡ ሁለት ወይም ሶስት እዚህ አሉ፡ እኔ... ለእነርሱ እናምናለን፡ ልጆች ናቸው፡ እነርሱም ደግሞ፡ ይፈወሳሉ። ደህና ይሆናሉ። አታምኑም? አሜን! "እነርሱ ይፈወሳሉ።" መፈወስ አለባቸው። እግዚአብሔር እንዲህ ብሏልና። እኛም ተጣበናል፡ እንደሚሆንም፡ አሁን እናምናለን።

181 አሁን፡ አገልግሎቶቻችን አንዱን ነገር ከሌላው በኋላ ወዲያውኑ ማካተትን ብቻ ያደርጋሉ። አሁን መሄድ ያለባቸውን ህዝብ እናሰናብታለን። ማየት እንደምችለው፡ ወደ አስር ሰዓት ለመድረስ ሰምንት ደቂቃ ያህል ይቀረዋል። እናም፡ መሄድ ካለባችሁም፡ እ—እዚህ በመገኘታችሁ በጣም ደስ ብሎናል፡ ዳግመኛም ተመልሳችሁ ከእኛ ጋር እንድትሆኑ እንፈልጋለን። የቀራችሁት፡ ከቆምን በኋላ፡ ዳግመኛ ትቀመጣላችሁ፥ የሚሄዱትም፡ በተቻለ መጠን በጸጥታ ይሂዱ። ከዚያም ወዲያውኑ የቅዱስ ቁርባን አገልግሎት ይኖረናል። መቆየት ከቻላችሁ እንድትቆዩ ተጋብዛችኋል። ካልቻላችሁም፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ጸልዩልኝ። እጸልይላችኋለሁ። እንዲሁም፡ አስታውሱ፡ ምልክቱን እንደተገበረ አቆዩት፡ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባትም ተጣበቡ። አሜን!

አሁን ከቻልን፡ መዝጊያ መዝሙራችንን እንዘምራለን፡ ሰንቆምም፡ **የኢየሱስን ስም ይዛችሁ ሂዱ**፡ እንዘምራለን።

> ... የኢየሱስ ስም ካንተ ጋር ውሰድ፡
> የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
> ደስታና ምቾት ይሰጣል... (አሁን ልታመጡት ትችላላችሁ።)
> ... በሄዳችሁበት አትለዩት።

ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ነው! (ኦህ ውብ ነው!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፥
ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም! (ውብ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

እርስ በርሳችሁ ተጨባበጡ፡ "መንገደኛ ወንድሜ፡ እህቴ፡ ጌታ ይባርካችሁ፡" ተባባሉ። በጥልቅ፡ በቅንነት፡ በአክብሮት፡ እንዲሁም ክርስቲያን ጓደኛሞች በህብረት ትስስር፡ ወንድሞችና እህቶች፡ እርስ በርሳችሁ ተጨባበጡ። እግዚአብሔር ሁላችሁንም፡ በአንድነት ይባርካችሁ። ድንቅ ነው!

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛው
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
በኢየሱስ እግር ላይ እስክንገናኝ፡ (እስክንገናኝ!)
እስክንገናኝ! ኦህ፡ እስክንገናኝ!
ዳግም እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን።

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
በኢየሱስ እግር ላይ እስክንገናኝ፡ (እስክንገናኝ!)
እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
ዳግም እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን።

182 ይህ ታላቁ የእግዚአብሔር ምልክት፡ መንፈስ ቅዱስ ጣፋጭነትና ህብረት፡ ዳግመኛ እስክንገናኝ ድረስ ከሁላችሁም ጋር በሙላት ይሁን። የእግዚአብሔር ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሂድ፡ ከፊታችሁም የሞትን መንገዶች ይምታ፥ ሁልጊዜም ኢየሱስን በፊታችሁ እንድታዩት፡ እንዳትናወጡም፡ መንገዳችሁንም የጠራ ያድርግ።

183 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ ይህንን አገልግሎት፡ የዛሬ ጠዋቱንም አገልግሎት፡ እነዚያን አገልግሎቶችና የተደረገውን ሁሉ፡ ለአንተ አሳልፈን እንሰጣለን፡ ክብርም ሁሉ ለአንተ ይሁን፡ ስዎችንም ስለፈወስክ፡ ሁላችንም የምንመለከተውን ያን ታላቅ ጸጋህንም ስለሰጠኸን ምስጋናችንና ውዳሴን ለአንተ እናቀርባለን። አድነን። ስለዚህ ነገር እንዴት እናመሰግንሃለን። ዳግመኛ እስክንገናኝ ድረስ አሁን ከእኛ ጋር ሁን። በቅዱስ ቁርባኑ ውስጥ ከእኛ ጋር ተገናኝ። ወደ ቤታቸው ለሚያሽከረክሩት፡ በመሪው ላይ ሁንላቸው፡ ጌታ ሆይ። ምንም አይነት ጉዳትና አደጋ እንዳይደርስባቸው፡ በዚህ ጥንቃቄ በጎደለው የበዓል ቀን ውስጥ ምራቸው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቀዋለን። አሜን።

መልካም፡ ዳግመኛ **የኢየሱስን ስም ይዛችሁ ሂዱ**።

ይዛችሁ… የኢየሱስን ስም…

አሁን በሰሙ፡ ተሰናብታችኋል።

… ካንተ ጋር፡

ወጥመድ ሲኖር ይታደግሃል፥
ፈተናዎች ሲከቧችሁ… (ከዚያስ ምን ታደርጋላችሁ? )
በጸሎት ቅዱስ ስሙን ተንፍሱ።

ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ነው! (ኦህ ውብ ነው!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ነው! (ኦህ ውብ ነው!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

በኢየሱስ ስም እየሰገድን፡
በእግሮቹ ስር በግንባራችን እየወደቅን፡
የነገሥታት ንጉሥ አክሊል ያጠልቃል፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ።

ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም! (ውብ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

184 አሁን ከመቀመጣችሁ ትንሽ ቀደም ብሎ፡ ህዝቡ አሁን ለቅዱስ ቁርባን አገልግሎት ጸጥ እያለ ባለበት ጊዜ።

ካልተሳሳትኩ፡ በቅርብ ጊዜ፡ አርካንሳስ ውስጥ ያገኘሁት አገልጋዩ ወንድም ብሌየር አይደለምን? እርሱ እንደሆነ አሰቤ ነበር። እርግጠኛ አልነበርኩም። ዛሬ ጠዋት፡ ትንሽ ልጅ፡ ለጌታ ለመስጠት ወደዚህ ይዘህ መጥተህ ነበር። አሰቤ ነበር… በቅርብ ጊዜ፡ እዚህ ሆት ስፕሪንግስ፡ አርካንሳስ አላገኘሁህም ነበርን? ከአንተ ጋር አንድ… አንድ ነገር ሊፈጠር ነበር፡ መንፈስ ቅዱስም ያንን ተናግሮት ነበር። ልክ ነበር? መልካም። ብቻ… ያን ጊዜ ወደ ኋላ መለስ ብዬ አሰብኩ፡ “ያ ወንድም ነው፡” ብዬም አሰብኩ። እዚህ በመሆንህ በጣም ደስ ብሎኛል፡ ወንድም ብሌየር።

185 አሁንም ሊደረግ ለተዘጋጀው የቅዱስ ቁርባን አገልግሎት እግዚአብሔር ንጹህ እንዲያደርገን እንዲጸልይ ወንድም ብሌየርን ልጠይቀው ነው። ትጸልያለህ፡ ወንድም ብሌየር? [ወንድም ሪቻርድ ብሌየር ጸለየ—አርታዒ።] አዎ። አዎ፡ ጌታ ሆይ። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። አዎ፡ ጌታ ሆይ። አዎ፡ ጌታ ሆይ። አዎ፡ ጌታ ሆይ። አዎ። አዎ። አሜን።

እያንዳንዳችሁ፡ አሁን መቀመጥ ትችላላችሁ።

186 አሁንም በኦርጋኑ ላይ፡ እህቴ፡ ሁላችሁም **በደም የተሞላ ምንጭ አለ** የሚለውን ብትጫወቱ። ከዚያም ልትጀምሩ… ወደዚያው ልትወስዷቸው ትችላላችሁ፡ እንዳስፈላጊነቱ። መልካም፡ አሁን ንባብ ይሆናል፡ ለአንድ አፍታ ብቻ… ጸጥ ብንል።

ምን አልሽ፡ እህቴ? [አንዲት እህት፡ “መሀረቤን ላምጣው” አለች? — አርታዒ።] መልካም፡ እህቴ፡ እስክታገኚው ድረስ በዚህ በኩል ብቻ ፈልጊ፡ ችግር የለውም፡ እዚያ ያለው ምንም ይሁን ምን። ያ ነው? መልካም፡ እህቴ።

187 መልካም፡ አሁን ወንድም ኔቪል የቅዱስ ቁርባኑን ስርአት ያነባል።

ቀጥሎም እዚህ እንግዶች ካሉ፡ አስተናጋጆች ወደ እያንዳንዱ፡ መቀመጫ ይመጣሉ፡ ስንመጣም፡ ለቅዱስ ቁርባኑ፡ በመተላለፊያ፡ እንዲሁም በተርታ ያመጣሉ።

188 አሁንም እንድታሰላስሉ እመኛለሁ። አስታውሱ፡ እስራኤል በመጣበብ በሉት፡ በአርባው አመት መጨረሻም በጉዞው ውስጥ በመካከላቸው፡ አንድም የደከመ አልነበረም። ይህም ደግሞ፡ መለኮታዊ ፈውስ ነው።

ጌታ ይባርክህ፡ ወንድም ኔቪል። [ወንድም ኔቪል አንደኛ ቆሮንቶስ 11፥23-32ን ያነባል—አርታዒ።]

**[ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን ከጌታ ተቀብያለሁና፡ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ፥]**

**[አመስግኖም፡ ቆረሰውና፡ እንዲህ አለ፡ እንካችሁ፡ ብሉ፥ ይህ ስለ እናንተ የሚቆረስ፡ ስጋዬ ነው፥ ይህንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።]**

**[እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንስቶ፡ ይህ ጽዋ፡ በደሜ የሚሆን፡ አዲስ ኪዳን ነው፥ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ፡ ይህንን፡ ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።]**

**[ይህንን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፡ ይህንንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ፡ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።]**

**[ስለዚህ ሳይገባው፡ ይህንን እንጀራ የበላ፡ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ፡ የጌታ ስጋና ደም እዳ አለበት።]**

**[ሰው ግን ራሱን ይፈትን፡ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ፡ ከጽዋውም ይጠጣ።]**

**[ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ፡ የጌታን ስጋ ስለማይለይ፡ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና።]**

**[ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፡ ያንቀላፉትም ብዙዎች ናቸው።]**

**[ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር።]**

**[ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ፡ ከአለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሰጻለን።]**

[ጌታ ንባቡን፡ ቃሉን ይባርክ።]

189 የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ የሚወክለውን፡ የኮሸር እንጀራን፡ የተጨማደደና የተሰበረን ይዣለሁ፥ በ—በዚህ በተቀደደው መጋረጃ በኩል ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግቢያ አለን።

190 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ ይህ እንጀራ ያንን የተሰበረውንና የተቀደደውን ስጋ ለመወከል ተዘጋጅቷል። እያንዳንዳችን፡ ስንቀበለው፡ ልክ ይህንን ድርጊት በአካል እንዳደረግነው ያህል ይሁንልን። የሀጢያታችንንም ስርየት፡ ወደ ቅድስተ

ቅዱሳን መግቢያንም እናገኝ ዘንድ፡ በወደፊቱ ህይወታችን በፊትህ እንድንኖር፥ በዚህ በምድር ላይ በምንኖርባቸው ቀናት ሁሉ፡ ከዘላለም እስከ ዘላለምም ከአንተ ጋር እንሆን ዘንድ ይሁንልን። አባት ሆይ፡ ይሁንልን። ይህንን እንጀራ ለታሰበለት አላማ ባርከው። በኢየሱስ ስም። አሜን።

191 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አለ፡ “እንጀራውን አንስቶ ከቆረሰ በኋላ፡ እንደዚሁም ጽዋውን አነሳ፥ ከእራትም በኋላ፡ እንዲህ ሲል፡ ‘ይህ ስለ እናንተ በሚፈሰው፡ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ጽዋ ነው።’” ስንጸልይም ጌታ በረከቱን በዚህ ላይ ያድርግ።

192 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ የወይኑን ደም፡ የወይኑን ጭማቂ እዚህ ይዣለሁ። አባት ሆይ፡ እኛን፡ የሚያነጻንን ያንን ክቡር ደም የሚወክል ነው፡ ያ ምልክት የመጣው ከዚያ ነው። አባት ሆይ፡ ስለዚህ ነገር፡ ስለዚሁ ምሳሌም አመሰግንሃለሁ። “ይህንን የሚበላና የሚጠጣ የዘላለም ህይወት አለው፡ በመጨረሻው ዘመንም ዳግመኛ አስነሳዋለሁ፡” ብለሃል። ስለዚህ ተስፋ እናመሰግንሃለን። እናም፡ አባት ሆይ፡ ልቦቻችንን በአንድነት፡ እንድታነጻ እንጸልያለን፡ በእምነታችን... የተገባን እንሆን ዘንድ፥ በራሳችን የተገባን እንዳልሆንን ብናውቅም፡ ነገር ግን እምነታችን አይወድቅም፡ ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን ደም በፍጹም ሁኔታ እየተቀበልን እንደሆነ ነው። አባት ሆይ፡ ይሁንልን።

193 ወይኑንም ለታሰበለት አላማ ቀድሰው። ዛሬ ማታ ይህንን ወይን የሚጠጣ ሁሉ፡ ከዚህም እንጀራ የሚወስድ፡ ከፊቱ ላለው ጉዞ ብርታት ይኑረው። ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን። ጤናማና ብርቱ ይሁኑ፡ ኢየሱስ እስኪመጣም ድረስ፡ በመንፈስህ ይሞሉ። አሜን።

194 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።] ቅዱስ ቁርባን በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ካሉት አምልኮዎች ሁሉ እጅግ ጥልቅ፡ የተቀደሰና፡ ጣፋጭ እንደሆነ አምናለሁ። ለእኛ የተተዉልን ሁለት ነገሮች፡ ልናደርጋቸው የሚገቡ፡ ሶስት ነገሮች ነበሩ፡ እ—እነዚያም ትእዛዛትና ሥርዓቶች ናቸው። በጣም ብዙ ሰዎች፡ “ዋናውን ሚስማር አግኝተናል” ለማለት ይሞክራሉ። “ከመስቀሉ ላይ አንድ ቁራጭ አግኝተናል” ይላሉ። ነገር ግን የተተዉ ሶስት ነገሮች ነበሩ፥ የጌታ እራት፡ ጥምቀት፡ እግር ማጠብ፡ ለቤተክርስቲያን የተተዉት ሶስት ትእዛዛት ነበሩ።

195 ለእኔም፡ የዛሬው ምሽት በጣም ልዩ ጊዜ ሆኖ ተሰምቶኛል። እዚህ ቆሜ ዝም ብዬ ሰመለከት፥ አብዛኛውን ጊዜ—ሁልጊዜ በጸሎት ላይ እሆናለሁ። ነገር ግን ዛሬ ማታ፡ የተለያዩ ቤተሰቦችን ስመለከት፡ አንዳንዶቹ ቤተሰቦች ገና ወጣት ሰባኪ ሆኜ፡ ያኔ የእንጨት ፍቅፋቂ በተሞላው ወለል ላይ እዚህ የነበሩ፡ እና እ... አንዳንዶቹም አዳዲስ ናቸው። ነገር ግን ሰዎቹ ከሚስቶቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሲመጡ መመልከት፡ እርስ በርሳቸውም እንዴት እንደሚከባበሩ ማየት፡ ያም ምን ያህል የተቀደሰ እንደሆነ፡ ልጆቻቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ ማየት፥ ያቺን ትንሽ እመቤት እጆቿን ስትዘረጋ ማየት፡ ደግሞም፡ “ያቺ እጅ ታጥባ፡ የህጻኑንም እንባ ከአይኖቹ ላይ ጠርጋለች” ብሎ ማሰብ የተለየ ያደርገዋል።

196 በዚያም ልጆቻቸው ትኩሳት ይዟቸው፡ ታመው በነበረ ጊዜ፡ ቤታቸው እንደነበርኩ የመጡ ቤተሰቦች አየሁ፥ ጌታ ኢየሱስ ልጆቻቸውን ሲፈውስ

አይቻለሁ። የቤተሰብ ችግር በገጠማቸው ጊዜ አየኋቸው፥ ጌታ ነገሩን እንዳስተካክለው ረድቶኛል፥ እንደገና ደስተኛ ሆነው አይቻቸዋለሁ። ወደዚያ ታላቅ የሰርግ እራት ስንሄድ እንዴት እንደሚሆን አስባለሁ። ጌታ ጓደኛችሁ እንድሆንና እንድረዳችሁ ስለፈቀደልኝ በጣም አመሰግነዋለሁ። እኔ… እዚህ ያለሁት ለዚያ ነው።

197 እኔም፡ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ አስባለሁ፡ ስንት ዓመታት፥ መሰበክ የጀመርኩት፡ በ1930 ገደማ፡ ነው፡ ሰላሳ-ሁለት ዓመታት ያህል ሆኖኛል፡ አሁን፡ ሰላሳ-ሦስት ዓመታት፡ ስሰብክ ነበር። ከዚያም፡ ትግሎችና ፈተናዎች ሁሉ፡ ምንም ቢመስል፡ ሆ—ሆኖም፡ እዚህ ሰ—ሰንመጣ፡ የተረሳ ይመስላል። አያችሁ? እ—እናንተ ስለ ጌታ እራት የሆነ ነገር ያለ ይመስል ነገሮችን ሁ—ሁሉ ትክክል ያደርጋል፡ የጌታ እራትን መውሰድ። ጌታ ይባርካችሁ።

198 አሁን ሽማግሌው ቀጥል፡ ለእግር-ማጠብ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱስን እንብብ።

199 [ወንድም ኔቪል ዮሐንስ 13፡ 2-17 አነበበ፡ አገልግሎቱንም ዘጋው—አርታዒ።]

**[እራትም ሲበሉ፡ ዲያብሎስ፡ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ፡ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ፥]**

**[ኢየሱስ አብ ሁሉን በልጁ እንደ ሰጠው፡ ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣ፡ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ አውቆ፥]**

**[ከእራት ተነሣ፡ ልብሱንም አኖረ፥ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ፡ ታጠቀ።]**

**[በኋላም በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ፡ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና፡ በታጠቀበትም ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ።]**

**[ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፥ እርሱም፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን አለው?]**

**[ኢየሱስም መልሶ፡ እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፥ በኋላ ግን ታስተውለዋለህ አለው።]**

**[ጴጥሮስም፡ የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው። ኢየሱስም፡ ካላጠብሁህ፡ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም ብሎ መለሰለት።]**

**[ስምዖን ጴጥሮስም፡ ጌታ ሆይ፡ እጄንና ራሴን ደግሞ እንጂ፡ እግሬን ብቻ አይደለም አለው።]**

**[ኢየሱስም፡ የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም፡ ሁለንተናው ግን ንጹሕ ነው፥ እናንተም ንጹሐን ናችሁ፡ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም አለው።]**

**[አሳልፎ የሚሰጠውን ያውቅ ነበርና፥ ስለዚህ፡ ሁላችሁ ንጹሐን አይደላችሁም አለው።]**

**[እግራቸውንም እጥቦ፡ ልብሱንም አንሥቶ፡ ዳግመኛ ተቀመጠ፡ እንዲህም አላቸው፡ ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን?]**

**[እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፥ እንዲሁ ነኝና፥ መልካም ትላላችሁ።]**

**[እንግዲህ፡ እኔ ጌታና መምህር ስሆን፡ እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርሰ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።]**

**[እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ፡ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።]**

**[እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም፥ መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም።]**

**[ይህን ብታውቁ፡ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ።]**

[ጌታ የቃሉን ንባብ ይባርክ።]

[በዚህ መካፈል ለሚፈልጉ ሁሉ፡ ወንዶች በዚህ ክፍል፡ እዚህ በኩል እግራቸውን ይታጠባሉ፥ ሴቶች ደግሞ በግራ በኩል ባለው ክፍል፡ እዚህ በመጥመቂያ ክፍል ውስጥ፡ ይታጠባሉ። ከእኛ ጋር መሳተፍ የሚፈልጉትንና፡ የሚችሉትን ያህል፡ ለማየት በጣም ደስተኞች ነን።]

[አብረን እንቁም? መሄድ ለሚገባቸው።]

[እንደገናም በዚህ መልካም ቀን፡ አምላካችን በእኛ መካከል መገኘቱንና፡ እኛን ለማበረታታትና ለመባረክ፡ እዚህ መገኘቱን በማየታችን በእግዚአብሔር ፊት በጣም አመስጋኞች ነን እንላለን።]

[ራሳችንን አብረን ዝቅ ስናደርግ፡ ወንድም አርል ማርቲን መሄድ የሚያስፈልጋቸውን እንዲያሰናብት እንጠይቀዋለን።]

63-0901E መጣበቦች
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው ® ።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org